ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ -አማርኛ ትምህርት ክፍል

# ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ተጠቅሞ ማስተማር የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ያለዉ ሚና (ከፊል ሙከራዊ ጥናት በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ

የሰውሀረግ ብርሃኑ ጎበና

በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነዘዴ የሁለተኛ ዲግሪ ለማሟላት የቀረበ ጥናት

ነሐሴ 2014 ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

**ጅማ ዩኒቨርሲቲ**

**ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**

ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ተጠቅሞ ማስተማር የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ያለዉ

ሚና(ከፊል ሙከራዊ ጥናት በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ

የሰዉሐረግ ብርሃኑ

አማካሪ፡-ማንያለዉ አባተ (ዶ/ር )

ረዳት አማካሪ፡- ለማ ንጋቱ (ዶ/ር)

በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነዘዴ የሁለተኛ ዲግሪ ለማሟላት የቀረበ ጥናት

ነሐሴ 2014 ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ምስጋና

በቅድሚያ እዚህ ያደረሰኝን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡ በመቀጠልም ከርዕስ መረጣ ጀምሮ ረቂቅ ጽሁፌን በማረምና አካሄዴን በማስተካከል አሁን ለደረስኩበት ደረጃ ላበቁኝ አማካሪዬ ለዶክተር ማንያለዉ አባተ እና ለረዳት አማካሪዬ ዶክተር ለማ ንጋቱ ልባዊ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነዉ፡፡ በመቀጠልም ይህን ጥናት እንድሰራ ባጀት በመመደብ ለረዳኝ ለጅማ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናዬ የላቀ ነዉ፡፡እንዲሁም ይህን ጥናት ባካሄዱኩበት ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር፤የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና ተጠኚ አስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላቅ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ የተለያየ ሀሳብ በመስጠት ለረዳኝ ባለቤቴ ዉብሸት በላይነህ እጅግ አመሰግናለሁ፡፡

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅሞ የመጻፍ ክሂልን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ያለዉ ሚና መለየት ነዉ፡፡ ጥናቱም ከፊል ሙከራዊ ሲሆን ፤ የተካሄደዉም በኦሮሚያ ክልል በኢሉባቦር ዞን በዳሪሙ ወረዳ በሚገኘዉ በዳሪሙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነዉ፡፡ በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ ተማሪዎች መካከል የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአመቺ የናሙና ስልት ከተመረጡ በኋላ ፤ በቀላል የእጣ ናሙና ስልት በሁለት መምህራን ከሚማሩ አምስት ምድብ ተማሪዎች በቀላል የእጣ ናሙና ስልት ሁለት ምድቦች ከተለዩ በኋላ በተራ የእጣ ናሙና ስልት አንዱ የሙከራ ሌላኛዉ የቁጥጥር ቡድን ሆኖ በጥናቱ ዉስጥ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ፈተና ስራ ላይ ዉለዋል፡፡ ፈተናዉ ፡-ቅድመ እና ድህረ ፈተናን ያካተተ ነዉ፡፡ ቅድመ ፈተናዉ የተሰጠበት አላማ ተማሪዎች ከሙከራ ጥናቱ በፊት ያላቸዉን የመጻፍ ክሂል ዉጤት ተቀራራቢ መሆን -አለመሆኑን ለመለየት ሲባል ነዉ፡፡ የድህረ ፈተናዉ አላማ ደግሞ የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድን ሆነዉ የተመረጡት ተማሪዎች በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች የመጻፍ ክሂልን ከተማሩ በኋላ በመካከላቸዉ ጉልህ ልዩነት መኖር - አለመኖሩን ለመለየት ነዉ፡፡ ተተኳሪ የሆኑት ተማሪዎች ከመጻፍ ልምምዱ በፊትና በኋላ ቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና ተፈትነዋል፡፡ ሁለቱም ቡድኖች የተፈተኑትን ፈተና በባእድና በጥንድ ቲ-ቴስት ስሌት ተሰልቶ ጉልህ የሆነ ልዩነት አሳይቷል፡፡በጥናቱ ግኝት መሰረት በግብ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅሞ የተማሩት የሙከራዉ ቡድን ተጠኚዎች ከቁጥጥር ቡድን ተጠኚዎች ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና ዉጤት በ 8.0926 አማካይ ዉጤት ብልጫ ማስመዝገባቸዉ፣ ብሎም በባእድና በጥንድ ናሙናዎች ተሰልቶ በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ዉጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ዉጤቱ (t=-2.799, df=60, p=0.001) አረጋግጧል፡፡ በዚህ መሰረት ግብ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅሞ የመጻፍ ክሂል ማስተማር በሰፊዉ ከተለመደዉ የመጻፍ ክሂልን ከማስተማር ዘዴ በመማሪያ መጽሐፍ በቀረቡ የመጻፍ ክሂል ተግባራት በተሻለ መልኩ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ዉጤት ለማሳደግ ሚና ያለዉ መሆኑን የጥናቱ ግኝት አመላክቷል፡፡ ይህም ዉጤት ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ተጥቅሞ የመጻፍ ክሂልን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል አኳያ ጉልህ ሚና እንዳለዉ ሊጠቁም ችሏል፡፡

**ማውጫ**

## Contents


ምስጋና ..... I

አጠቃሎ ..... II

ማውጫ ..... III

የሰንጠረዥ ማውጫ ..... V

ምዕራፍ አንድ ..... 1

መግቢያ ..... 1

፲.፲.የጥናቱ ዳራ ..... 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ..... 4

1.3 የጥናቱ መላምት ..... 4

1.4. የጥናቱ አላማ ..... 5

1.4.1. አብይ አላማ ..... 5

1.4.2. ዝርዝር አላማ ..... 5

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ..... 5

1.6.የጥናቱ ወሰን ..... 5

1.7.የጥናቱ ውስንነት ..... 5

1.8 የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት ፍች ..... 6

ምዕራፍ ሁለት ..... 7

ክለሳ ድርሳናት ..... 7

2.1. የንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ..... 7

2.1.1. የመጻፍ ክሂል ምንነት ..... 7

2.1.2. የፅሀፈት ትምህርት አስፈላጊነት ..... 8

2.1.3 የመጻፍ ትምህርት አላማዎች ..... 10

2.1.4 የመጻፍ ክሂልን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ምክንያቶች ..... 10

2.1.7 የጽሀፈት ክሂል ምዘና ..... 18

2.2.ጥናቱ የሚከተለው የንድፍ ሀሳብ ማእቀፍ ..... 20

2.3.የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ..... 21

ም ዕራፍ ሶስት .......... 22
የጥናቱ ንድፍና የአጠናን ዘዴ.......... 22
3.1.የጥናቱ ንድፍ .......... 22
3.2. የጥናቱ አካላይ.......... 22
3.3. የናሙናዎች አመራረጥ .......... 22
3.3.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ .......... 22
3.3.2. የክፍል ደረጃ አመራረጥ እና የተጠኚዎች ናሙና አመራረጥ .......... 22
3.4 የትምህርት ይዘት አመራረጥ .......... 23
3.5 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ.......... 24
3.6 ፈተና .......... 24
3.7 የመረጃ አተናተን.......... 24
ምዕራፍ አራት.......... 25
የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ .......... 25
4.1. የጥናቱ ውጤት ትንተና .......... 25
4.2.የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ.......... 29
ምዕራፍ አምስት .......... 31
ማጠቃለያ መደምደሚያ የመፍትሄ ሀሳቦች እና የጥናት ጥቆማዎች .......... 31
5.1 ማጠቃለያ .......... 31
5.2 መደምደሚያ.......... 32
5.3 የመፍትሄ ሀሳቦች.......... 32
5.4 የጥናቱ ጥቆማዎች.......... 32
ዋቢዎች.......... 33
አባሪ-1 .......... 36
አባሪ-2 .......... 38
አባሪ-3 .......... 40

## የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 4.1፡- የተተኳሪ ቡድኖች ቅድመ ፈተና ውጤት ንጽጽር /በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት/...............................25

ሰንጠረዥ 4.2፡- የተተኳሪ ቡድኖች ድህረ የመጻፍ ክሂል ውጤት ንጽጽር/ በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት/......................26

ሰንጠረዥ 4.3፡- የሙከራ ቡድን ቅድመና ድህረ የመጻፍ ክሂል ውጤት ንጽጽር/ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት/..........................................................................................................................................27

ሰንጠረዥ 4.4፡-የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ውጤት ንጽጽር / በጥንድ ናሙናቲ-ቴስት/.........................................................................................................................28

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1.የጥናቱ ዳራ

ጽህፈት የአንድን ቋንቋ አጠቃቀም ሙሉዕ ከሚያደርጉት ዋና ዋና ክሂሎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በመጻፍ ክሂል የአንድን ቋንቋ ተጠቃሚ የሚፈልገውን መልእክት ያስተላልፋል እንዲሁም መልእክት ይቀበላል (Harmer፣1991) ፡፡
መጻፍ የስሜት ህዋሳትን በማቀናጀት በርካታ ባህርያትን በአንድ ጊዜ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወን ውስብስብ የአእምሮ ስራ ነው (Nunan፣1998) ፡፡ ጽህፍት የንግግር ድምጾችን የሚወክሉ ትዕምርቶችን በመጠቀም አሳብን በወረቀት ላይ የማስፈር ሂደት ነው (Harmer፣1991) ፡፡ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ደግሞ ብዙ ተግባራትን መወጣትን ይጠይቃል፡፡
እንደ (አማረ፣ 2010) አስተያየት የሀሳብ አደረጃጀት፣የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣የአረፍተ ነገር አወቃቀር እና የአንቀጽ አመሰራረት ለክሂሉ በዋነኝነት ከሚያስፈልጉ ጉዳዮች ዉስጥ የሚጠቀሱ ናቸዉ፡፡

መላኩ (2013) እንደሚያስረዱት የቋንቋ ትምህርት ትኩረት የሚያደርግባቸዉ ይዘቶች መካከል አንዱ የመጻፍ ክሂል ነዉ፡፡ ቀደም ባለዉ ዘመን መጻፍ ልክ እንደ እጅ ጥበብ ሙያ ይቆጠርና ከሌሎች ትምህርት ዘርፎች ማለትም ሂሳብ ፣ ሳይንስ፣ ፍልስፍና … ወዘተ ጋር ተጣምሮ ይሰጥ ነበር (Rimes;1983)፡፡እንዲሁም ሰዋስዉና ቃላትን ለመማር አጋዥ እንደነበር እና እራሱን እንደ ቻለ ክሂል እንደማይታይ በመቀጠልም የመጻፍ ክሂል ራሱን ችሎ መሰጠት የተጀመረዉ በ20ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን ገደማ ነዉ፡፡ አነሳሱም በወቅቱ የነበረዉ የመጻፍ አቀራረብ በተማሪዎች የእጅ ጽሁፍ የመጨረሻ ረቂቅ ማስተካከል አረፍተ ነገሩን በሚገባ የማዋቀርና በቋንቋዉ ህግ ላይ ያተኮረ እንደነበረ ገልጸዋልClark(2003),andKroll (1990);Rimes(1983) እንደሚገልጹት የመጻፍ ክሂል ሃሳብ በማፍለቅ ካንባቢ ጋር የሚያግባባ የተማሪዎችን የአስተሳሰብ አድማስ የሚያሰፋ እና እንደ አንድ የመማሪያ ዘዴ ሆኖ የሚያገለግል ነዉ፡፡ ይህም ክሂሉ በቋንቋ ትምህርት ዉስጥ ትኩረት እንዲሰጠዉ ምክንያት ሆኗል፡፡ እንዲሁም የመጻፍ ክሂል አፈፈቶችም ሆነ ኢ-አፈፈቶች በመደበኛ የመማር አዉድ የሚያዳብሩት ከመሆኑም ባሻገር በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደት ጽህፈትን ተጠቅሞ ለማወቅ ተገቢነት እንደ አለዉ ያስረዳሉ (Brown, 1994)፡፡

የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ከምንጠቀምባቸዉ የማስተማሪያ ዘዴዎች ወይም አቀራረቦች መካከል ዉጤት ተኮር እና ሂደት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴዎች የሚጠቀሱ ናቸዉ፡፡ እንደ Meriwether(1977) አገላለጽ ዉጤታዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች በቅድሚያ የመጻፍ ሂደቶችን ተከትለዉ እንዴት መጻፍ እንዳለባቸዉ እንዲማሩ ሳይደረግ በቀጥታ

የተሟላ ጽሁፍ ጽፈዉ እንዲያቀርቡ የሚጠበቅበት እና መምህራን በቀረበዉ ጽሁፍ ዉስጥ ያለዉን የይዘት እና የቅርጽ ትክክለኛነት የሚገመግሙበት ነዉ፡፡

Silva(1993) በበኩላቸዉ በተለምዷዊ ሁኔታ የሚከናወን ወይም ያላንዳች እዉቀት እና ግንዛቤ የአንድን ተቋም እቅድ እና አሰራር ስልት ከመቅዳት ጋር የሚመሳሰል ተግባር የሚገልጽ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

አማርኛ በሁለተኛ ደረጃ  ትምህርት ቤቶች በትምህርትነት ከሚሰጥባቸው አጠቃላይ አላማዎች ውስጥ አንዱ ተማሪው የቋንቋውን ስርአት ጠብቆ ሃሳቡን  በጽሁፍ መግለጽ የሚችል እንዲሆን ማስቻል ነው (የአምላክስራ፣2008) ፡፡

መጻፍየ ክሂል እንደ ሁለተኛ ወይም በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ የበታች እንደሆነ ተደርጎ ይታያል (White: 1994) :: ጽህፈት የሚጠቅመው በንግግር መልክ የተማሩትን  ቋንቋ  ለማጠናከር ነዉ (Byrne- 1991):: በአማርኛ ትምህርታቸው ውስጥ ከሚማሯቸው ይዘቶች አንዱ የጽህፈት ክሂል ነው፡፡ ተማሪዎች የተሻለ የመጻፍ  ክሂል እንዲያጎለብቱ  ተገቢ የጽህፈት ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የጽሁፍ ትምህርት ለተማሪዎች በተገቢው መንገድ እንዲሰጥ ከተፈለገ ሌሎች በርካታ ጉዳዮች እንዳሉ ሆኖ የክፍል ውሰጥ የመማር ማስተማር ሂደት ዋናው አካል ድግሞ መምህራንና ተማሪዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት ዋናው ትኩረቱ  መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ተጠቅመው ተማሪዎችን የጽህፈት ክሂል ለማሻሻል ያለው ሚና መለየት ነው፡፡ ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ  አዲስ የዳበረ ነው፡፡ እድገቱ በሂደት ላይ የተመሰረተ ትምህርት ማስተማር ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ግብ ተኮር ትምህርት በሶስት ዋና ዋና ደረጃዎች የተዋቀረ ነው፡፡ ሀ. ጽንሰ ሀሳቦችን ለመገንባት እና ለማገናኘት ምልከታ እና መግለጫ (observation and description to build ad connect concepts) ፣ ለ. ጽብረቃ (reflection) ሐ. በምክንያታዊነት ግብ ማውጣት (setting a goal with reasining) ናቸው፡፡

እንደ ርእሰ ጉዳዮች ይህ ተጨማሪ እርምጃዎችን በመጨመር ወይም ደረጃዎቹን በመድገም ሊራዘም ይችላል፡፡ለምሳሌ ራስን በመመልከት እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን በመመልከት ምልከታውን የበለጠ ሊከፋፈል ይችላል፡፡

ጽንሰ ሀሳብ ከተፈጠረ በኋላ ፣ ጽንሰ ሀሳቦቹ ትልልቅ ጽንሰ ሀሳቦችን ለመስራት አንድ ላይ ሊገናኙ ይችላሉ፡፡ መጀመሪያ ላይ ጽንሰ ሀሳቦችን ለመፍጠር እና ለማገናኘት በአንድ ወይም በሁለት እውቀት ሊጀምሩ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን አስተማሪዎች ከማስተማሪያ ቁሳቁሶች አዲስ እውቀት በመጨመር የጽንሰ ሀሳብ  እና የጽንሰ ሀሳብ ግንኙነት  ማስፋት ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች ገና ከጅምሩ ከፍተኛ መጠን ያለው እንዲያካሂዱ ቢጠይቁ በጣም ይገርማሉ፡፡ ስለዚህ በጣም ውጤታማው መንገድ በትንሹ መጀመር እንደ ክር መስራት አንድ በአንድ ይጨምሩ፡፡ ጽንሰ ሀሳቦች በመድገም እና በማገናኘት፣ አስተማሪዎች ተማሪዎችን የበለጠ እውቀት እንዲጠቀሙ ሊመሯቸው ይችላሉ፡፡ በዚህ ሂደት ተማሪዎች የተገነቡ እና የተገናኙ ጽንሰ ሀሳቦች እንዲገልጹ ማድረግም አስፈላጊ ነው፡፡ መግለጫው አመክንዮዎቹ እንዲታዩ ጽንሰ ሀሳቦቹን በምስል ማሳየት ነው፡፡ ይህ ጽንሰ ሀሳቦቹ እንዴት እደተገነቡና የተገናኙትን ጽንሰ ሀሳቦች እንዲገለጹ ማድረግም አስፈላጊ ነው፡፡  ይህ ጽንሰ ሀሳቦቹ እንዴት እንደተገነቡና እነደተገናኙ እንዲመለከቱ አስተማሪዎች ናቸዉ፡፡ ተማሪዎች ጽንሰ ሀሳቦችን ከምልከታ ጀምሮ በትንሹ ድጋፍ ቢሹ መገንባት እና ማገናኘት ይችላሉ፡፡

ተማሪዎች ግቦችን ለማውጣት ደረጃ 1. የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት (እውቀትና ክህሎት)፡፡ ደረጃ 2. ተማሪዎች ምሳሌን እንዲመለከቱ ማድረግ (ተማሪዎች እንዲያነቡ ጠይቅ፣ ቪዲዮዎችን ወይም ሌሎች የቀረቡ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ይመልከቱ)፡፡ ደረጃ 3. ተማሪዎች ምልከታቸውን እንዲገልጹ ጠይቋቸው (ይህ የእውቀት ጽንሰ ሀሳብ ሂደት ነው)፡፡ ደረጃ 4. ተማሪዎች ከደረጃ ሶስት ጽንሰ ሀሳቦችን እዲያገናኙ ይጠይቁ እና ይግለጹ፡፡ ደረጃ 5. ከደረጃ አራት ማብራሪያውን በማንጸባረቅ ተማሪዎች ጥያቄዎችን እንዲያቀርቡ ይጠይቋቸው፡፡ ደረጃ 6. ከደረጃ አምስት ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ተማሪዎች ግቦችን እንዲያወጡና ጥናታቸውን እንዲነድፉ ጠይቅ፡፡

ነገር ግን እውቀትን እና ክህሎቶችን ከማቅረብ በተቃራኒ እያንዳንዱን እርምጃ ማከናወን ያለባቸው ተማሪዎች መሆን አለባቸው፡፡ የአስተማሪዎች ሚና የተማሪዎችን ግብአቶች (እውቀት እና ክህሎቶች ለተማሪዎች እንዲጠቀሙበት) እና መመሪያ መስጥት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ አውቀት እና ችሎታዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ ግን ዋና ትኩረት አይደሉም፡፡ ዋናው ትኩረት በእውቀትና በክህሎት ግብን የማውጣት ሂደት ነው፡፡ ይህ ከፕሮጀክት- ተኮር ትምህርት ጋር መምታታት የለበትም፡፡ አስተማሪዎች ተማሪዎች እንዲያከናውኑ ፕሮጀክት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ግቡን ያማከለ የማስተማር ዘዴ ተማሪዎች ከጥናት በፊት ያለውን ግብ በራሳቸው የማውጣት ችሎታ እንዲያዳብሩ ነው፡፡

ከግብ ተኮር የማስተማር ሂደት ውስጥ በጣም ፈታኙ እርምጃ ግብ ለማውጣት ጥያቄዎችን መፍጠር ነው፡፡ምክንያቱም አብዛኛው ተማሪዎች በእውቀት እና በክህሎት ላይ የተመሰረተ ትምህርት ስላለፉ እና ይህም ተማሪዎችን እንዳይጠይቁ ስለሚያደርግ ነው፡፡ በእውቀትና በክህሎት ላይ ያተኮረ ትምህርት ተማሪዎችን በእውቀት ወይም በክህሎት ትክክለኛነት ይገመግማል፡፡ ግምገማው ትክክለኛ መልሶች ላይ ያተኮረ ሲሆን ተማሪዎች በተለይ ጥያቄው ትክክለኛው ጥያቄ ስለመሆኑ ሲጠራጠሩ ጥያቄዎችን መጠየቅ አይችሉም፡፡ ግብ ለማውጣት ጥያቄዎች መሆን አለባቸው ምክንያቱም ግብ ማለት ያልተገለጸ ወይም ገና ያልተገኘ ማለት ነው ( international journal for infonomics(IJI), volume 13, issue 2, 2020)፡፡ ተማሪዎች በመጻፍ ክሂል ትምህርት የሚጠበቀውን ያህል ለውጥ እንዲያመጡ የትምህርቱ አቀራረብ እና ትምህርቱ የሚሰጥበት የማስተማሪያ ዘዴ ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡ በመሆኑም በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የመጻፍ ክሂል ትምህርት ከግብ የሚደርሰው የትምህርቱ ይዘት ተገቢ የማስተማሪያ ዘዴን በመጠቀም ማቅረብ ሲቻል እንደሆነ ማገሬ (2008) እነ Hawanm (2005), Vaner (1974) ን በመጥቀስ ገልጻለች፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

መጻፍ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች አንዱ ሲሆን የሰው ልጅ ሀሳቡንና ስሜቱን ለመግለጽ ፣ መልእክት ለማስተላለፍ ፣ በአለም ላይ የሚፈጸሙ ሁነቶችን በተመለከተ መረጃ ለመለዋወጥ ፣ ስለራሱም ሆነ ስለሌሎች በጥልቀት ለመረዳት፣ ባህልን፣ ወግንና ታሪክን በሰነድነት በማስቀመጥ ለመጭው ትውልድ ለማቆየት የሚያገለግል መሳሪያ እንደሆነ Heawan (2005) ፣ Miller (1999) ፣ Hedge (1998) እና Riamis (1983) በመጥቀስ ገልጽዋል፡፡

ይሁን እንጂ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ትምህርት ትኩረት እንዳነስውና በዚህም ረገድ የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ደካማ እንደሆነ (ማረው ፣ 2005 ፣ አምሳሉና ደምሴ ፣ 1982 ፣ አለማየሁ ፣ 1986 ፣ ደረጄና ግርማ ፣ 1999) ገልጸዋል፡፡

የመጻፍ ክሂል ማስተማር በኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ልምድ ቢኖርም እስካሁን የታለመለትን ግብ በሚጠበቀው መጠን ተሳክቶ አይታይም፡፡ ለዚህም ችግር ዋና ዋና የሚባሉት መምህራን የሚከትሉት የማስተማር ስልት፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት፣ የተማሪዎች ፍላጎት ማጣት፣ የክፍለ ጊዜ እጥረት እና የተማሪዎች ቁጥር መብዛት ናቸው (ተስፋዬ፣1981) ፡፡

ይህን ጥናት ለማካሄድ የተፈለገበት ዋናው ምክንያት አጥኝዋ መደበኛ ስራዋን በምትሰራበት ዳሪሙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመጻፍ ክሂላቸው ዝቅተኛ በመሆኑ በአማርኛ ቋንቋ ግብ ተኮር ማስተምሪያ ዘዴ መጠቀም የመጻፍ ክሂልን ለማሻሻል ያለውን ሚና ለመለየት በማሰብ ነው፡፡ ስለዚህ ይህን ጥናት ግብ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ በአማርኛ ቋንቋ መጠቀም የጽህፈት ክሂል ለማሻሻል ያለው ሚና በሚል ርእስ ከፊል ሙከራዊ ጥናት በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት ለማካሄድ አጥኝዋ በመነሳሳት ጥናቱን አካሂዳለች፡፡ ምክንያቱም ይህ ማስተማሪያ ዘዴ በቅርብ ጊዜ ስራ ላይ የዋለ ስለሆነ በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ያለው ሚና አልተጠናም፡፡

## 1.3 የጥናቱ መላምት

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የመጻፍን ክሂልን ለማሻሻል ያለዉን ሚና መፈተሽ ነዉ፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱ የሚከተሉትን መላምቶች አስቀምጧል፡፡

ግብ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ የአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂልን ለማሻሻል ሚና አለው፡፡

ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂልን ለማሻሻል ሚና የለውም፡፡

## 1.4. የጥናቱ አላማ

### 1.4.1. አብይ አላማ

የዚህ ጥናት አብይ አላማ ግብ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ያለውን ሚና ማሳየት ነው፡፡

### 1.4.2. ዝርዝር አላማ

ከዚህ በላይ ያለውን አብይ አላማ ለማሳካት የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ተካተዋል፡-

ተማሪው ግብ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅሞ መማሩ የመጻፍን ክሂል ለማሻሻል ያለው ሚና መለየት፡፡

ተማሪዉ ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ተጠቅሞ መማሩ ያስገኘለት ሚና መግለጽ፡፡

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

በዚህ ጥናት የሚገኘው ውጤት አወንታዊ ከሆነ የሚከተሉት ጥቅሞች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡ መምህራን ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማጎልበት ያለውን ጥቅም እንዲገነዘቡት ያደርጋል፤ ለአማርኛ ቋንቋ ስረአተ ትምህርት አዘጋጆች ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ያለውን ሚና ያሳያል እንዲሁም በዚህ ርዕስ ዙሪያ ጥናት ለሚያጠኑ እንደ መነሻ ሀሳብ በመሆን ያገለግላል፡፡

## 1.6.የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ግብ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ተጠቅሞ የመጻፍ ክሂልን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ያለው ሚና ላይ ያተኩራል፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልል በኢሉባቦር ዞን በዳሪሙ ወረዳ በ 2014 ዓ.ም በዳሪሙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚማሩ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ ሌሎች የክፍል ደረጃዎችን አይመለከትም፡፡ ምክንያቱም ጥናቱ ከፊል ሙከራዊ በመሆኑ አጥኝዋ መደበኛ ስራዋን በምትሰራበት የጥናቱን ተሳታፊዎች በቅርበት ለማግኘትና ለማከናወን ስለሚያስችል ተመራጭ ሆኗል፡፡ ማሬ (2008)፣ Gham and Perin (2007) ን ጠቅሳ እንደገለጸችው የመጻፍ ትምህርትን አስመልክቶ የሚደረጉ ጥናቶች በመካከለኛ የክፍል ደረጃዎች ላይ በርካታ ስራዎች ቢሰሩ ተማሪዎቹ እያደጉ በሚሄዱበት ጊዜ ችሎታቸውን እያሻሻሉ ይሄዳሉ የሚል አተያይ በመኖሩ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት የተካሄደው በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት ነው፡፡

## 1.7.የጥናቱ ውስንነት

የዚህ ጥናት ትኩረት ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የመጻፍ ክሂልን ለማሻሻል ያለዉ ሚና በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የፈተሸ ሲሆን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዉ የችሎታ መለኪያ ፈተና ነዉ፡፡ ለትምህርት የተመረጡት የሁለት ክፍል ተማሪዎች ማለትም የ"C"እና "E"ክፍል ተማሪዎች አጠቃላይ ድምር ዘጠና ስድስት ተማሪዎች ተመርጠዉ ትምህርቱን በመከታተል ላይ እያሉ ፈተና ከመጀመሩ በፊት ሰላሳ አራት ተማሪዎች አቋርጠዋል፡፡ በዚህ ችግር ምክንያትም ለዚህ ጥናት ተሳታፊዎች የሆኑት ስልሳ ሁለት ተማሪዎች ብቻ መሆናቸዉ ይህ ጥናት ዉስንነት ታያቶበታል፡፡

## 1.8 የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት ፍቺ

**የመጻፍ ክሂል**፡- የቋንቋዉን ስርአት በጠበቀ መልኩ ሀሳብን ወይም ስሜትን በጽሁፍ መግለጽ ማለት ነዉ፡፡

**ግብ ተኮር፡-**በእዉቀትና በክህሎት ላይ ያተኮረ ትምህርት ተማሪዎችን በእዉቀት ወይም በክህሎት

ትክክለኛነት መገምገም ማለት ነዉ፡፡

**ኢ-ርቱእ የጽህፈት ምዘና፡-**ምርጫ ነክ ምዘና(ምርጫ የሚሰጥ)

**ርቱእ የጽህፍት ምዘና፡-**በጻፉአቸዉ ጽሁፎች ላይ እንዲተነትኑ የሚያደርግ

**ግብ**፡-ያልተገለጸ ወይም ገና ያልተገኘ ማለት ነዉ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምእራፍ ውስጥ የዚህ ምርምር ምንነት ለመገንዘብ እና ለመረዳት የሚያስችሉ የተለያዩ ድርሳናት ተከልሰው ቀርበዋል፡፡ በዚህም የንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት፣ የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት ማለትም የጽሁፍ ምንነት፣ የጽህፍት ትምህርት አስፈላጊነት፣ የጽህፈት ክሂል ማሪሚያ ዘዴ ፣ የጽህፍት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች እና የቀደምት ስራዎች ቅኝት የሚሉ ንኡሳን ክፍሎች ተካተው እደሚከተሉት ቀርበዋል፡፡

## 2.1. የንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

የመጻፍ ክሂል በባህሪው ክሂለ ብዙ ነው፡፡ የሀሳብ አደረጃጀት፣ የአንቀጽ አመሰራረጥ፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀር፣ የቃላት አመራረጥ እና አጠቃቀም ለመጻፍ ክሂል ትምህርት ከሚያስፈልጉ ክሂሎች መካከል በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ ማረው (2003) ፡፡

ክሂሉ እየጻፉ መማርንም ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ በቀጥታ ወደ መጻፍ ስራ ከመግባታቸው በፊት በሂደቱ ላይ ብዙ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለአብነት የሚከተሉትን ሂደቶች በቅደም ተከተል ማለፍ ይኖርባቸዋል፡፡

ለምን እንደሚጽፉ በውል መገንዘብ ፤ ለማን እደሚጽፉ ለይቶ ማወቅ ፤በምልከታ፣ በማስታወሻ በመመዝገብ፣ እርስ በርስ በመወያየትና በማንበብ አስፈላጊ መረጃዎችን ማሰባሰብ ፤እንዴት መጻፍና መረጃዎችን አንዴት ማደራጀት እንዳለባቸው የስራ እቅድ ማውጣት ፤የመጀመሪያ ረቂቅ መንደፍ ፤ረቂቁን መገምገም፣ መከለስ ፤በርካታ ረቂቆችን በተደጋጋሚ ካዘጋጁ በኃላ የመጨረሻውን ጽሁፍ መጻፍ ፤ለመጨረሻ ጊዜ እንደገና በጥልቀት አንብቦ መገምገም፡፡

በአጠቃላይ የመጻፍ ክሂልን ለማለማመድ ግራፎችን፣ ችግሮችና መፍቴዎችን፣ በጅምር የቀሩ አንቀጾችን፣ የአንቀጽ ቅደም ተከተላቸው የተዛባ ድርሰቶችን፣ የአረፍተ ነገር ቅደም ተከተላቸው የተዛባ አንቀጾችን ወዘተ መሰረት በማድረግ መስራት ይቻላል ማረው (2003) ፡፡

እንዲሁም የጽህፈት ችሎታን ለማሳደግ ለተማሪዎች መነሻ የሚሆን ሞዴል ይቀርብላቸዋል፡፡ ከዚያም የቀረበላቸውን የጽሁፍ ሞዴል የቅርጽ፣ የይዘት እና የአደረጃጀት ባህሪያት ለማጥናት ጽሁፉን ይተነትናሉ፣ በተጨማሪም ልሳናዊ ጉዳዮችንና ቅንብራዊ አሰዳደሮችን ይለያሉ፡፡ የቀረበላቸውን ሞዴል ካጠኑና የቋንቋውን አለባዊያን ከለዩ በኋላ ተመሳሳይ ጽሁፍ ለመጻፍ መነሻ የሚሆን አዲስ ግብአት ይሰጣቸዋል፡፡ በአጠቃላይ በውጤት ተኮር ዘዴ አመለካከት የጽህፈት ችሎታ አስቀድሞ በአረፍተ ነገር ወይም በዲስኩር ደረጃ የተሰጡ ስደራዎችን ተከትሎ ትክክለኛ የቋንቋ ቅርሶችን የማዘጋጀት አቅም ተደርጎ ይታያል በለጠ (2006) ፡፡

### 2.1.1. የመጻፍ ክሂል ምንነት

መጻፍ የስሜት ህዋሳቶችን በማቀናጀት በርካታ ባህሪያትን በአንድ ጊዜ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወን ውስብስብ የአእምሮ ስራ ነው (Nunan፣1998) ፡፡ ጽህፈት የአንድን ቋንቋ አጠቃቀም ሙሉዕ ከሚያደርጉት ዋና ዋና ክሂሎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በጽህፈት ክሂል የአንድን ቋንቋ ተጠቃሚ የሚፈልገውን መልእክት ያስተላልፋል እንዲሁም መልእክት ይቀበላል (Harmer፣1991) ፡፡

ጽህፈት የንግግር ድምጾችን የሚወክሉ ትምህርቶችን በመጠቀም አሳብን በወረቀት ላይ የማስፈር ሂደት ነው (Harmer፣1991) ፡፡ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ደግሞ ብዙ ተግባራትን መወጣት ይጠይቃል፡፡

የሀሳብ አደረጃጀት፣ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም ፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀር ፣የአንቀጽ አመሰራረት ለክሂሉ በዋነኝነት ከሚያስፈልጉ ጉዳዮች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው (አማረ፣ 2010) ፡፡

አማርኛ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በትምህርትነት ከሚሰጥባቸው አጠቃላይ አላማዎች ውስጥ አንዱ ተማሪው የቋንቋውን ስርአት ጠብቆ ሃሳቡን በጽሁፍ መግለጽ የሚችል እንዲሆን ማስቻል ነው (የአምላክስራ፣2008) ፡፡

የጽህፈት ክሂል እንደ ሁለተኛ ወይም በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ የበታች እንደሆነ ተደርጎ ይታያል (White: 1994):: ጽህፈት የሚጠቅመው በንግግር መልክ የተማሩትን ቋንቋ ለማጠናከር ነው (Byrne- 1991):: በአማርኛ ትምህርታቸው ውስጥ ከሚማሯቸው ይዘቶች አንዱ የጽህፈት ክሂል ነው፡፡ ተማሪዎች የተሻለ የመጻፍ ክሂል እንዲያጎለብቱ ተገቢ የጽህፈት ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የጽሁፍ ትምህርት ለተማሪዎች በተገቢው መንገድ እንዲሰጥ ከተፈለገ ሌሎች በርካታ ጉዳዮች እንዳሉ ሆኖ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ዋናው አካል ድግሞ መምህራንና ተማሪዎች ናቸው፡፡ ተማሪዎች በመጻፍ ክሂል ትምህርት የሚጠበቀውን ያህል ለውጥ እንዲያመጡ የትምህርቱ አቀራረብ እና ትምህርቱ የሚሰጥበት የማስተማሪያ ዘዴ ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡ በመሆኑም በክፍል ውስጥ ሚሰጠው የመጻፍ ክሂል ትምህርት ከግብ የሚደርሰው የትምህርቱ ይዘት ተገቢ የማስተማሪያ ዘዴን በመጠቀም ማቅረብ ሲችል እንደሆነ ማሬ (2008) እነ Hawanm (2005), Vaner (1974) ን በመጥቀስ ገልጻለች፡፡

ጽህፈት በእይታዊ ትእምርቶች ውክልና በመገልገል ሰዎች ሃሳብ የሚለዋወጡበትና ተራክቦ የሚመሰርቱበት ተግባቦታዊ መሳሪያ ነው፡፡ በመተላለፊያ ስልቱ ዕይታዊ፣ በአካላዊ ተግባቦታዊ አፍላቂ፣ በተግባቦታዊ ባህሪውም ርቱዕ ክሂል ነው (Widdowson፡1978፣ Harmer፡ 1991)፡፡ ጽሁፍ ተማሪዎች በተጨባጭ እውቀትና በአእምሮ ሂደት ውስጥ ሃሳብ፣ ፍላጎት፣ ልምድ፣ መልእክት፣ እና አመለካከታቸውን በቃላት የሚያስተላልፉበት የቋንቋ ክሂል ነው ( Karimu፡2004) ፡፡

ጽህፈት ሃሳብን በትእምርት ወይም በቋንቋ የመወከል ሂደት ነው፡፡ ሂደቱም አካልንና አዕምሮን በማቀናጀት በአንድ ጊዜ በርካታ በሀሪያቱን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወንና ከማሰብ ጋር የተቆራኘ ውስብስብ የአእምሮ ስራ ነው (Nunan፡ 1989)

ከዚህ እንደ ምንረዳው ጽህፈት በትምህርት የሚዳብር በተከታታይ ሙከራ የሚጎለብት የሰው ልጅ አእምሮዉንና አካሉን በማስተባበር ዕውቀቱን፤ ገጠመኙን፤ ሀሳቡንና ውስጣዊ ስሜቱን በተገቢ ድምጻዊ ምልእክቶችን በመወከል ለመሰሎቹ የሚያስተላልፍበት መንገድ ነው፡፡

## 2.1.2. የፅህፈት ትምህርት አስፈላጊነት

ተማሪዎች መፃፍ ከመጀመራቸዉ በፊትም ሆነ በሚጽፉበት ጊዜ የጽህፈት ተግባቦት ዓላማ ለይቶ በማወቅ ክሂሉን ባግባቡ መጠቀም እንዲችል በቂ የጽህፈት ትምህርት ያስፈልገዋል፡፡ በትምህርቱም ወቅት ለምን እንደሚጽፍ፣ ለማን እንደሚጽፍ፣ እንዴት እንደሚጽፍ፣ በመጠየቅ እንደሚጻፍበት አላማ የመጻፍ ክሂሉን የሚያዳብረው ጽህፈትን ሲማር ነው Wigard (1986) ፡፡ ጽህፈትን መማር ተማሪዎች ሌሎች የትምህርት አይነቶችን እንዲማሩ ከማገዙ በላይ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ

አገባቦችና አገላለጾችን፣ ፈሊጣዊ አባባሎችና ቃላትን እንዲያውቁ ከመርዳቱም በላይ በተማሪዎች ዘንድ የ መማር ተነሳሽነትን ይፈጥራል Raimis (1985) ፡፡

በተጨማሪም የጽህፈት ክሂል ትምህርት ተማሪዎች በቃል የሚሰጣቸውን ትምህርት አዳምጠው የተለያዩ ጽሁፎችን አንብበው ማስታወሻ እንዲይዙና በቤት ስራና በክፍል ውስጥ የሚሰጡትን አዳምጠውና የተለያዩ ፅሁፎችን አንብበው ማስታወሻ እንዲይዙና በቤት ስራ በክፍል ውስጥ የሚሰጡትን ፅሁፍ-ነክ መልመጃዎችን በጽሁፍ አቀነባብረው መግለጽ ያስችላቸዋል Venkateswaram (1995) ፡፡

Hamil (1986) የድርሰት ትምህርት ሶስት ጠቀሜታዎች እንዳሉት ይገልጻል፡፡ እነሱም ተማሪዎች ቢያንስ በስረአተ ትምህርቱ መሰረት በትምህርት ቤት የሚሰጡ ትምህርቶችን ለመከታተል ፤ ተማሪዎች በጽህፈት ቅርፆችን በማስተማር ከትምህርት ቤት ዉጭ በሚሰሩ ስራዎች ማለትም ደብዳቤ መፃፍ፣ ማመልከቻ መፃፍ፣ ቅፆችን መሙላት፣ ማስታወሻ መያዝ የመሳሰሉ ጉዳዩችን ላይ ችሎታ እንዲኖራቸው ያደርጋል በተጨማሪም ተማሪዎች የፈጠራ ፅሁፎችን ማለትም ግጥሞችን፣ ልቦለዶችን፣ ታሪኮችን መጻፍ እንዲችሉ ያደርጋቸዋል፡፡

እንደ Heaten (1991) ጽህፈትን ማስተማር የሚከተሉትን ችሎታዎች ለማዳበር እንደሚቻል ይገልጻሉ፡፡እነሱም ማስተላለፍ ለሚፈልጉት ሀሳብ ተገቢ የሆነ ስልቶችን የመምረጥ፣ የአረፍተ ነገር አመሰራረት የአንቀጽ አወቃቀር ስረአት ጠብቆ የመጻፍ፣ የተለመደና መደበኛ ቋንቋ የመጠቀም ብቃትን ያዳብራል ፤ ሰዋስዋዊ ክሂሎችን በመማር ተገቢ የሆኑ አረፍተ ነገሮችን መስርቶ የመጻፍ ብቃትን ያጎለብታል ፤ ግላዊ ስሜትን ለመግለጽ የሚያስችሉ አረፍተ ነገሮችን የማፍለቅ ችሎታን ያዳብራል ፤ ተገቢ የሆኑ ቃላትን በመምረጥ አላማን ወስኖ ለአንባቢ የማቅረብ ብቃትና የሀሳብ አደረጃጀትን ትክክለኛነትን ጠብቆ መረጃዎችን በቅደም ተከተል አቀናብሮ የመግለጽ ችሎታን የዳብራል ፤ የጽሁፍ ቋንቋ መገለጫ የሆኑትን ስረአተ አፃፃፍ ደንቦች ተገንዝቦ በተገቢው መንገድ በአገልግሎት ላይ የማዋል ብቃትን ያስገኛል እንዲሁም ለማስተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ተገቢና ተስማሚ የሆኑ ቃላትን መርጦ ማስተላለፍ፣ የሃሳብ አቀራረብን፣ ሚዛናዊነትን ጠብቆ ክንዉኖችን ወይም ክስተቶችን በቅደም ተከተል አቀነባብሮ የመግለፅ ችሎታ ማዳበር የሚሉት ናቸው፡፡

መጻፍ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች አንዱ ሲሆን የሰው ልጅ ሀሳቡንና ስሜቱን ለመግለጽ፣ መልእክት ለማስተላለፍ፣ በአለም ላይ የሚፈጸሙ ሁነቶችን በተመለከተ መረጃ ለመለዋወጥ፣ ስለራሱም ሆነ ስለሌሎች በጥልቀት ለመረዳት፣ ባህልን፣ ወግንና ታሪክን በሰነድነት በማስቀመጥ ለመጭው ትውልድ ለማቆየት የሚያገለግል መሳሪያ እንደሆነ  Heawan (2005) ፣ Miller (1999) ፣ Hedge (1998) እና Riamis (1983) በመጥቀስ ገልጽዋል፡፡

ይሁን እንጂ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ትምህርት ትኩረት እንዳነሰውና በዚህም ረገድ የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ደካማ እንደሆነ (ማረው፣2005፣አምሳሉና ደምሴ፣1982 ፣ አለማየሁ፣1986 ፣ደረጀና ግርማ፣1999) ገልጸዋል፡፡

የመጻፍ ክሂል ማስተማር በኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ልምድ ቢኖርም እስካሁን የታለመለትን ግብ በሚጠበቀው መጠን ተሳክቶ አይታይም፡፡ ለዚህም ችግር ዋና ዋና የሚባሉት መምህራን የሚከትሉት የማስተማር ስልት፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት፣ የተማሪዎች ፍላጎት ማጣት፣ የክፍለ ጊዜ እጥረት እና የተማሪዎች ቁጥር መብዛት ናቸው (ተስፋዬ፣1981) ፡፡

### 2.1.3 የመጻፍ ትምህርት አላማዎች

የመጻፍ ትምህርት አላማ በቀዳሚነት የሚያተኩረዉ ተማሪዎች በድርሰት አማካይነት ሀሳባቸዉን በተቃናና በተዋበ መንገድ መግለጽ እንዲችሉ ማገዝ ላይ ነዉ:: በዚህ ሀሳብ ላይ Raimes (1983,4 ) ሀሳባቸዉን ሲሰነዝሩ፣ ተማሪዎች መጻፍን የሚማሩባቸዉ ዓላማዎች አረፍተ ነገር ከመጻፍ በዘለለ መልኩ ሊታዩ የሚገባቸዉ መሆናቸዉን ገልጸዉ፣ ዓላማዉ የሚያካትታቸዉን ዋና ዋና ነገሮችም ሲዘረዘሩ ከአንባቢያን ጋር በጽሀፈት አማካይነት ተግባቦትን መፍጠር በዕለት ተዕለት የህይወት ገጠመኞች የሚከሰቱ ክስተቶችን መዝግቦ ማቆየት፤ በቋንቋ ዉስጥ ያሉ የጽሁፍ ዉህድ አሃዶችን በይበልጥ በአገልግሎት ለመጠቀም መለማመድ ናቸዉ በማለት አለምነሽ (2011) Raimes (1983፣4 ) ን በመጥቀስ ገልጻለች ::

በተመሳሳይ Lee (1997፣ 73-76) የመጻፍ ትምህርት ዓላማን አስመልክተዉ ሲገልጹ ደግሞ ከሁሉም በፊት ለተማሪዎች መጻፍን የምናስተምርበት ዋናዉ ዓላማ ተማሪዎች በስልጣኔ እየዳበረ ከመጣዉ የዓለማችን ሁኔታ ጋር ተጣጥመዉ እንዲሄዱ ለማድረግ ነዉ:: የትምህርቱ ዓላማም ይህንን የመጻፍ ትምህርት ከግብ ለማድረስ የሚያግዝና በማስተማር ስልቶች ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባዋል ይላሉ:: በተጨማሪም ይህ የመጻፍ ትምህርት ዓላማ በሶስት አቅጣጫዎች ሊታይ እንደሚገባዉ ይገልጻሉ::

አንደኛ ሰዋዊ የሆኑ ፍላጎቶችን የሚሟላት ዓላማ፣በዚህ ዉስጥ የእርስ በርስ ሀሳብን የመለዋወጥ ሁኔታዎችና ነገሮችን ማከናወን ይካተታል:: ለምሳሌ:- ለብዕር ጓደኛ ደብዳቤ መጻፍ የመሳሰሉትን ያካትታል:: ሁለተኛ እዉቀት ላይ ያተኮሩ ዓላማዎች፣ በዚህ ዉስጥ መረጃዎችን የመተርጎም፣ የመጠቀም፣ ሀሳቦችን አስፋፍቶ የመግለጽ እና በተግባር በመጠቀም ነገሮችን የመፍታት ሁኔታዎች ይካተታሉ:: ለምሳሌ:- ሪፖርት መጻፍና የመሳሰሉት በዚህ ስር ይካተታሉ እና ሶስተኛው ደግሞ ልምድን የሚመለከቱ ዓላማዎች፣ በዚህ ዉስጥ እዉነተኛ ለሆነና ምናባዊ ለሆኑ ልምዶች ምላሽና ማብራሪያዎችን መስጠት ይካተታል:: ለምሳሌ:- ግጥም መጻፍ የመሳሰሉት በዚህ ዉስጥ ይመደባሉ::

በአጠቃላይ ተማሪዎች መጻፍን የሚማሩበት ምክንያት በደብዳቤ ወይም በማስታወሻ ሀሳብን በመለዋወጥ ወይም ከሰዎች ጋር ለመግባባት ሲሆን ይህም ሰዋዊ የሆነዉን አቅጣጫ የሚያመለክት ነዉ:: ሀሳቦችንና እዉነታዎችን በመመዝገብ በግራፍና በቻርት መረጃዎችን ወደ ጽሁፍ መለወጥና በጽሁፍ ማብራራት፣ ሀሳብን በቅደም ተከተል መግለጽና ለመማሪያነት መጠቀም፣ ችግሮችን መፍታት፣ ወዘተ... የመሳሰሉት ከእዉቀት አቅጣጫ የሚታሰቡ ናቸዉ:: በጥልቀት ማሰብና ስሜትን መግለጽ ደግሞ ከልምድ አቅጣጫ የሚታዩ ናቸዉ::

### 2.1.4 የመጻፍ ክሂልን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ምክንያቶች

ቱሉ (2014 ) ምሁራንን በመጥቀስ እንደ ገለጸዉ Rechards (1974:100)" ቁጥራቸዉ ይህ ነዉ የማይባል ተማሪዎች ለጽሁፍ ፍራቻ እና ጭንቀት ይታይባቸዋል "ሲሉ ይገልጻሉ::ይህ ችግር እስካሁን እስከ ዩኒቨርሲቲ ዘልቆ ለመከሰቱ በርካታ ምክንያቶች እንዳሉ በሙሁራኑ ተገልጿል(Ellis 1989,Richards 1974,Norish 1983)::ከችግሮቹም ዋና ዋና የሚባሉት መምህራኑ የሚከተሉት የማስተማር ስልት፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት፣ የተማሪዎች ፍላጎት ማጣት፣የክፍለ ጊዜ እጥረት እና የተማሪዎች ቁጥር መብዛት ናቸዉ(ተስፋዬ፣1981):: በተጨማሪም መጻፍ ለብዙዎች

አስቸጋሪ የሚሆንበትን ምክንያትByrne (1997:4) ሲያስረዱ ሶስት ምክንያቶች ይጠቅሳሉ፡፡ እነሱም ስነልቦናዊ ችግር፣ ሰዋስዋዊ ችግር እና ገንዛቤያዊ ችግር ናቸዉ፡፡

መጻፍ ከንግግር የበለጠ ስነልቦናዊ ጫና ያሳድራል፡፡ (Byrne(1997:4) እንደ ሚያስረዱት ንግግር ተፈጥሯዊ፣ በየትኛዉም ሁኔታ እና አጋጣሚ የምንጠቀመዉ የመግባቢያ መንገድ ነዉ፡፡ በየትኛዉም ቦታና ሁኔታ ዉስጥ ስንናገር ስህተት ብንፈጽም ከአድማጭ እርማት እናገኛለን፣ ሀሳባችንን በጽሁፍ ስንገልጽ ግን ያለማንም እገዛና ያለምንም ማስተካከያ በራሳችን የምንወጣዉ ተግባር ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ የስነልቦና ጫና ስለሚያሳድር መጻፍን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

እንደ Byrne (1997; 4-5) ገለጻ በንግግር ወቅት ገለጻ ስናደርግ አድማጭ ንግግራችን እንዲቀጥል ያግዘናል፡፡ ንግግራችን ላይ ችግር (ስህተት) ቢፈጠር እየደገምን ወደ ኋላ እየተመለስን አስተካክለን መቀጠል እንችላለን፡፡ በጽህፈት ጊዜ ግን እነዚህ ሁሉ ዕድሎችአይኖሩም፡፡ ተግባቦታችን በራሳችን ችሎታና እዉቀት ብቻ የተገደበ ይሆናል፡፡ በራሳችን የቃላት ምርጫ፣ በራሳችን የቃላት መዋቅር፣ አረፍተ ነገሮችን መመስረት ይጠበቅብናል፡፡ ከዚህ ሂደት በኋላ የጻፍነዉ ጽሁፍ በአንባቢ ይተረጎማል፡፡ ይሄ ደግሞ ሌላዉ ጽህፈትን አስቸጋሪ የሚያደርገዉ ነገር ነዉ፡፡

እንደቀደሙት ሁሉ በዚህም ጊዜ ንግግር መልዕክት ለማስተላለፍ ያለ ማንም ጋባዥ፤ ያለ ማንም አስገዳጅነት በራሳችን ፍላጎት እና ባሻን ጊዜ የምንጠቀመዉ መግባቢያ ነዉ፡፡ ይህ ደግሞ ምንም አይነት ትምህርትና እዉቀት አያስፈልገዉም፡፡ መጻፍ ግን በመደበኛ መንገድ የምንማረዉ፣ የራሱ ህግና ስርአት ያለዉ መግባቢያ ነዉ፡፡ የቋንቋዉን የጽህፈት ህግ በሚገባ ማወቅ ይጠይቃል፡፡ የቋንቋዉ የጽህፈት ህግ ብቻ ሳይሆን ሀሳባችንን በጽሁፍ እንዴት መግለጽ እንዳለብንና ከአንባቢያችን ጋር ያለምንም ችግር እንዴት መግባባት እንደምንችል ማወቅ ይኖርብናል፡፡ ይህ ሶስተኛዉ የመጻፍን ክሂል አስቸጋሪ የሚያደርገዉ ሂደት ነዉ በማለት (Byrne 1997:5) አብራርተዋል፡፡

የመጻፍ ትምህርት አቀራረቦች (Writing Approaches)

የቋንቋን ትምህርት ለማስተማር መምህራንን በጋራ የሚያስማማ ወጥነት ያለዉ አንድ ብቸኛና የታወቀ ዘዴ የለም፡፡ ቢሆንም ግን እንደማንኛዉም ስራ የመጻፍ ትምህርትም የራሱን ዕቅድ ተከትሎ ቢከናወን የተሻለ ዉጤት ላይ መድረስ እንደሚቻል የመስኩ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ለዚህም ደግሞ ምንድነዉ የምንጽፈዉ? ለማን ነዉ የምጽፈዉ? መቼ ነዉ የምጽፈዉ? ሀሳቦችንና መረጃዎችን የት ነዉ የማገኘዉ? እንዴትስ ነዉ የማደራጀዉ? ለሚሉት ጥያቄዎች በቅድሚያ ምላሽ መስጠት እንደ ሚያስፈልግ ማረዉ (1992) ያስረዳሉ፡፡

ተማሪዎች በመጻፍ ክሂል አስፈላጊዉን የባህሪ ለዉጥ እንዲያሳዩ በማድረግ ረገድ መምህራን የሚጠቀሙበት የትምህርት አቀራረብ የላቀ ድርሻ አለዉ፡፡ የመጻፍ ትምህርት አቀራረቦች፣ ስነ ዘዴዎችና አመለካከቶች በመማር ማስተማሩ ሂደት ዉስጥ የየራሳቸዉ ስልቶች አሏቸዉ፡፡ ትኩረት ከሚሰጡት የጽሁፍ ባህርይ አኳያ በተለያዩ ምሁራን በልዩ ልዩ ስያሜዎች ይገለጻሉ፡፡ ከነዚህ ዉስጥ በመስኩ ሙሁራን ተደጋግመዉ የሚጠቀሱትና ተቀባይነት ያገኙት የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ከሚያገለግሉ

አቀራረቦች መካከል የጽህፈትን ክሂል ለማስተማር የሚያገለግሉ የተለያዩ ዘዴዎች ቢኖሩም በአሁኑ ጊዜ ግን ተቀባይነትን አግኝተው በስፋት እየተሰራባቸው ያሉት ሁለት መሆናቸውን የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡እንዚህም፡-

**ውጤታዊ አቀራረብ (product approach )**

ውጤታዊ አቀራረብ ከረጅም ጊዜ አንስቶ ጽህፈትን በማስተማር ሲያገለግል የኖረና በአሁን ጊዜም ለተለያዩ አላማዎች በማገልገል ላይ ያለ ነው፡፡ ይህ አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ተማሪዎች በሚጽፉት ጽሁፍ የመጨረሻ ውጤትና በቋንቋው ቅርጽ ላይ ነው (Richard፣ 1990)፡: ይሄውም ተማሪዎች ለሚጽፏቸው ድርሰቶች ምሳሌ ይሆናሉ ተብለው የሚታሰቡ ጽሁፎችን በሞዴልነት አቅርቦ ሰዋስዋዊ ህጎችን፣ አደረጃጀትን፣ የአጻጻፍ ብለሀትን ወዘተ በማሳየት ተማሪዎች እነዚያኑ አስመስለው እንዲጽፉ የሚያለማምድ ነው (Nunan 1989 and Richard 1990) ፡፡

በዚህ አቀራረብ ጽህፈትን በማስተማር ሂደት በየደረጃው የተለያዩ ተግባራት ይከወናሉ፡፡ እነዚህም ተግባራት ውስን ጽህፈት፣ ምር ጽህፈትና ነጻ ጽህፍት ደረጃዎች ናቸው፡፡

በዉጤታዊ አቀራረብ ጽህፈትን በማስተማር ሂደት በየደረጃዉ የተለያዩ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ እነዚህም ተግባራት ዉስን ጽህፈት፣ምር ጽህፈትና ነጻ ጽህፈት ደረጃዎች ናቸዉ (pincas, 1982; 14, Raimes, 1983, 7; Richards, 1990; 107)::

**ሀ.ዉስን ጽህፈት**

ለመጀመሪያ ደረጃ የቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ለማካሄድ የጽህፈት ትምህርት የሚቀርብና የዉስንነት ደረጃዉ ፍጹም ወይም አንጻራዊ የሆነ ክንዉን ነዉ፡፡ የዚህ የጽህፈት ስራ ዋና ዓላማ ተማሪዎች አንጻራዊ በሆነ መንገድ ከስህተት የጸዳ ጽሁፍ እንዲጻፍ ማድረግ ነዉ፡፡ በዉስን የጽህፈት ደረጃ ጽህፈትን ለማስተማር የሚቀርቡት ይዘቶች ዉስን መሰብንና ማፍለቅን የሚጠይቁ ናቸዉ፡፡ በዉስን ጽህፈት ደረጃ ባዶ ቦታዎችን መሙላት፣በሰንጠረዥ የቀረቡ ቃላትን በማቀናጀት ዓረፍተ ነገር መስራት፣ቅደም ተከተላቸዉ የተፋለሰ ቃላትን በማስተካከል ዓረፍተ ነገር መስራት፣በአንቀጽ ዉስጥ፣የቁጥር፣የጾታ፣የጊዜ ወዘተ ለዉጥ በማድረግ እንደገና መጻፍ የመሳሰሉት ይገባቸዋል(Doff,1988እና Kroll)::

**ለ. መር ጽህፈት**

መር ጽህፈት በዉስንና በልቅ ጽህፈት መካከል እንደ ድልድይ ሆኖ የሚያገለግል ነዉ፡፡ ይኸዉም ተማሪዎች በዉስን ጽህፈት ደረጃ ካዳበሩት መሰረታዊ የዓረፍተ ነገር የአጻጻፍ ክሂል በተጨማሪ የአጻጻፍ ስልት ለመለየት የሚያግዙና ወደ ነጻ የሚያሸጋግሩ ይዘቶችን የሚይዝ በመሆኑ ነዉ፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች መምህራን በሚየቀርቡላቸዉ ሞዴል መሰረት የጽህፈት ልምድ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ደረጃ የሚካሄዱ ዉይይቶች ድርሰትን ለመጻፍ የሚያገለግሉ ምር የጽህፈት ተግባራት መሆናቸዉን Doff (1988,62) Raimes (1983,103) እና Princas (1982,102 ) ይገልጻሉ፡፡

### ሐ. ነጻ ወይም ልቅ ጽህፈት

በዚህ ደረጃ ተማሪዎች በአብዛኛዉ መምህራን በሚሰጣቸዉ ወይም ራሳቸዉ በመረጡት ርዕስ ዙሪያ ሀሳብ አፍልቀዉ በራሳቸዉ ቋንቋና አገላለጽ ድርሰት የሚጻፍበት ነዉ (Pincas,1982 እና Raimes,1983)::ድርሰት የመጻፍ ስራ የሚጀምረዉ የቋንቋዉን ሰዋስዋዊ ቅርጾች በመለማመድ ነዉ፡፡ ከልምምድ ቀጥሎ ለሚጻፉት የድርሰት አይነት ሞዴል ይቀርባል፡፡ ነጻ ጽህፈት ለሰዋስዋዊ አጠቃቀም እና ለስርዓተ አጻጻፍ ትኩረት የሚሰጥ፣እንዲሁም በትክክለኛነት ላይ የሚያተኩር ቢሆንም፣ ተማሪዎች የራሳቸዉን ሀሳብ የሚገልጹበት እድል ይሰጣል፡፡ Raimes (1983;7 ) ነጻ ጽህፈት ተማሪዎች ሀሳባቸዉን ለመግለጽ የሚጽፉበት ደረጃ በሆንም የጽሁፋቸዉ መለኪያ ምን፣እንዴት፣ለማንና ለምን ተጻፈ? የሚሉት ጥያቄዎች ሳይሆኑ የሚነሱት ሰዋሰዋዊ ስህተቶች ያልበዙበት ጽሁፍ ቀረበ ወይ? የሚለዉ ነዉ፡፡ በመሆኑም የተማሪዎቹ ትኩረት የሚያርፈዉ ሀሳባቸዉን በመግለጽ ላይ ሳይሆን በጽሁፋቸዉ ጥራት ወይም ንጽህና ላይ ነዉ (Byren, 1991; 16 እና Pincas, 1982)::

በዉጤታዊ አቀራረብ የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ የመምህሩ ሚና በአብዛኛዉ የቋንቋዉን ሰዋስዋዊ ህጎችን ማስተማር፣የተማሪዎችን የመጨረሻ ዉጤት ሰብስቦ ሰዋሰዋዊ ስህተቶችንና የአጻጻፍ ስርዓተ ግድፈቶችን ማረም፣ የጽሁፉን ጥሩነትና መጥፎነት ከትክክለኛነት አንጻር መገምገም፣ ለመማር የሚያበረታታ አስተያየት ወይም ዉጤት መስጠት ነዉ፡፡

በዉጤታዊ አቀራረብ ጽህፈትን ለማስተማር የሚዘጋጅ መምህር ተማሪዎች ዉጤታማ እንዲሆኑ ተገቢዉን ዝግጅት ሊያደርግ እንደሚገባ Byrne (1988) Pincas ፣(1982) ፣ Atkins (1995) እና ሌሎች የሚከተሉትን ነጥቦች በመዘርዘር ይገልጻሉ፡፡

ለጽህፈት ክሂል የተመረጡት መልመጃዎች ለተማሪዎች ቀርበዉ ከመተግበራቸዉ በፊት ተገቢነታቸዉን፣ ቀስቃሽነታቸዉን፣ ግልጽነታቸዉንና ለአዉዱ ተገቢ መሆናቸዉን ያረጋግጣል ፤ መልመጃዎች ግልጽ መመሪያ ያላቸዉና ከሌሎች ክሂሎች ጋር ቅንጅት ያላቸዉ መሆኑ ያሳዉቃል ፤ የቋንቋዉን ሰዋስዋዊ ህግጋት ለተማሪዎች በማሳወቅ በጽሁፋቸዉ ዉስጥ እንዲጠቀሙ ያደርጋል ፤ ተማሪዎች ለጽህፈት ትምህርት ቅድመ ዝግጅቶች የሚያደርጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡

**ሂደታዊ አቀራረብ(process approach) ፡፡**

በዚህ አቀራረብ ስልት ትኩረት የሚያደርገው በድርሰቱ የመጨረሻ ውጤት ላይ ሳይሆን ከመጀመሪያ ጀምሮ በጽህፈት ወቅት በሚከናወኑ ተግባራት ወይም ወደ ውጤት ለመድረስ በሚያስችለው ሂደት ላይ ነው፡፡ በሂደታዊ አቀራራብ የጻፊው ትኩረት ስለሚጽፈው ጽሁፍ አላማና ስለ ተደራሲዎቹ ሳይሆን ጽሁፉን እዴት እንደ ሚጀምርና እነዴት እደሚያደራጀው በመወሰን ላይ ነው (Raimis; 1983) ፡፡

በዚህ አቀራረብ ጽህፈትን በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ልዩ ልዩ የጽፈት ደረጃዎችን ያልፋሉ ፡፡ እነዚህ የአጻጻፍ ደረጃዎች ቅድመ ጽፈት፣ ጊዜ ጽፈት እና ድህረ ጽፈት ናቸው

በሂደታዊ አቀራረብ ጽህፈትን በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች በተለያዩ አቀራረብ የጽህፈትን ተግባራትን ለማከናወን ልዩ ልዩ የጽፈት ደረጃዎችን ያልፋሉ፡፡ እነዚህ የአጻጻፍ ደረጃዎች Richards(1990,112).Hedge(1988,22-24) እና Raimes(1983,69) ቅድመ ጽህፈት፣ ጊዜ ጽህፈት፣ እና ድህረ ጽህፈት በማለት በሶስት ሲከፍሏቸዉDukes(1983)እና Murras(1982) ደግሞ የማሰላሰል፣ የማርቀቅና የክለሳ ደረጃ በማለት ይገልጻቸዋል፡፡

**ሀ. ቅድመ ጽህፈት ደረጃ**

ቅድመ ጽህፈት የማሰላሰል ደረጃ ሲሆን፣መጻፍን ከመጀመር በፊት የሚከናወን ዝግጅቶችን በሙሉ ይይዛል፡፡ ይኸዉም ተማሪዎች ሀሳባቸዉን የሚያሰባስቡበት፣ እቅዳቸዉን የሚነድፉበትና በአጠቃላይም ወደ ዋናዉ የጽህፈት ደረጃ ለመግባት የሚዘጋጁበት ሂደት ነዉ፡፡ ስለምን ልጻፍ? እና እንዴት ልጻፍ? የሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙበት በዚህ ክፍል ነዉ፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች በመረጡት ርዕስ ላይ ከክፍል ጓደኞቻቸዉ ጋር በመሆን ይነጋገራሉ፡፡ መምህራን ለተማሪዎች መመሪያ በመስጠት የሚጽፉትን ርዕስ ጉዳይ በሚገባ እንዲያዉቁት ይመራሉ፣ ይከታተላሉ (Murray,1982;Hedge,1988 እና Richards,1990)::

**ለ. ጊዜ ጽህፈት**

ጊዜ ጽህፈት የማርቀቅ ደረጃ ሲሆን፣በዚህ ደረጃ ሀሳብ በማፍለቅ ጊዜ የተሰበሰቡ መረጃዎችን የማመቻቸትና የመጀመሪያ ረቂቅ መጻፍና የተጻፈዉን የማንበብና የመከለስ፣ ጽሁፍ የሚዳብርበትን ሀሳብ የመፈለግ ተግባር ይከናወናል፡፡ ተማሪዎች በዚህ ጊዜ ለሰዋስዋዊ ስህተቶች አይጨነቁም፣ሀሳብ እንደመጣላቸዉ ይጽፋሉ፣የማይፈልጉትን ሀሳብ አስወጥተዉ አዲስ ሀሳብ መተካት ይችላሉ፡፡ በጊዜ ጽህፈት ቅድሚያ የሚሰጠዉ ለይዘት ትክክለኛነት ሲሆን፣በቀጣይ በሚጽፉት የድርሰት ረቂቅ ላይ ከይዘት ባሻገር ተማሪዎች የተጠቀሙባቸዉን ስርዓተ ነጥብ፣ሰዋስዉን፣የሆሄያት አጣጣልን፣ወዘተ የመመርመርና የማስተካከል ተግባርን ያከናዉናሉ (Hedge,1991)::

**ሐ.ድህረ ጽህፈት**

የክለሳ ደረጃ ሲሆን፣ ጸሀፊዉ የጽሁፉን መልዕክት፣ ቅርጹንና ተደራሲዉን ደግሞ የሚያስብበት፣ የመልዕክቱን ግልጽነት የሚገመግምበትና የመጨረሻ ማስተካከያ የሚጽፍበት ደረጃ ነዉ፡፡ በዚህ ደረጃ ላይ ጸሀፊዉ ድህረ ጽህፈት በጽሁፍ ዉስጥ ለአንባቢያን ያስቸግራሉ የሚላቸዉን የተለያዩ ቃላትን ለይቶ በማዉጣት ማስተካከያ ይሰጣል፡፡የተጻፈዉን ጽሁፍ ከሰዋስዉ፣ ከስርዓተ ነጥቦችና ከሀሳብ አደረጃጀት አኳያ የሚመረምርበት በዚህ ደረጃ ነዉ፡፡

በሂደታዊ አቀራረብ የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ የመምህሩ ሚና በሂደታዊ አቀራረብ ጽህፈትን የሚያስተምር መምህር ለተማሪዎች የእርስ በርስ መማማር ወይም ተራክቦ ቦታዉን እንደሚለቅ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ በዚህም መሰረት መምህራን መማርን የማመቻቸትና የመከታተል ፣የተማሪዎችን የጹሁፍ ተግባቦታዊ ክህሎች የማዳበር፣ የተማሪዎችን ጽሁፍ የማንበብ፣

የመገምገምና የማማከር፣ እንዲማሩ የማገዝ፣ መማርን የማፋጠን Ruddeg(1999) ;Scrivene (1994 );Hedge (1991,7) እና Leki (1994,57 ) ሚና ይጫወታል፡፡

ሂደታዊ የጽህፈት አቀራረብ በክፍል ዉስጥ በሚተገበርበት ጊዜ የመምህሩን የማስተማር ዘዴ በተመለከተ Richards (1990, 111) የሚከተለዉን ሀሳብ ያቀርባሉ፡፡በሂደታዊ አቀራረብ መምህሩ ተማሪዉን እንደ ዉጤታዊ አቀራረብ ዘዴ ያለቀለት ስራ እንዲያቀርብ የተወሰነ ነገር የሚጠይቀዉ ሳይሆን፣ ተማሪዉ ትክክለኛ ጽሁፍ፣ ለመጻፍ የሚያስችለዉን ዘዴ የሚቀይስና የሚያመቻች እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

**የማስተማሪያ ዘዴ አስፈላጊነት**

በአጠቃላይ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በክፍል ውስጥ ይተገበራሉ፡፡ለምሳሌ የሚከተሉት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

***መምህር ያተኮር ማስተማሪያ ዘዴ* (teacher- cented instruction)፡**

*በዚህ ማስተማሪያ ዘዴ መምህራን የክፍል ሀላፊዎች ናቸው፤እና ሁሉንም እንቅስቃሴዎች ይመራሉ፡፡በተለምዶ በዚህ አቀራረብ ተማሪዎች ከመምህሩ ጋር ፊት ለፊት በተያያዙ ጠረጴዛዎች ላይ ተቀምጠዋል፡፡ የቡድን ስራ ሊካሄድ ቢችልም አብዛኛው የክፍል ጊዜ ከመምህሩ ጋር ጽንሰ ሀሳቦችን በማብራራት እና የግለሰብ ስራን ይመድባል፡፡*

*የዚህ ማስተማሪያ ዘዴ ጠቀሜታ፤ የአስተማሪውን የአመቻችነት ሚና አስፈላጊነት ያጎላል ፤በባህሪ ንድፈ ሀሳብ ላይ የተገነባ ነዉ፡፡*

*የዚህ ማስተማሪያ ዘዴ ደካማ ጎኑ፤ የተማሪ መነሳሳት ማነስ ፤ ተማሪዎች የራሳቸውን ምርጫ እንዳያደርጉ በቂ እድል አለመስጠቱ*

**አነስተኛ ቡድን *መመሪያ* (small group instruction)፡**

*አብዛኛውን ጊዜ የቡድን ትምህርትን ይከተላል እና ለተማሪዎች የተቀነሰ የተማሪ መምህር ጥምርታ ይሰጣል፣ በተለይም ከአራት እስከ ስድስት ተማሪዎችን በቡድን ያሳትፋል፡፡*

*ጠቀሜታው- ትምህርቶቹ ከየአንዳንዱ ተማሪ ደረጃ ጋር ይጣጣማል ፤ የተማሪዎች መሀበራዊ መላመድ ክሂሎችን ያበረታታል*

*ጉዳቶቹ- ደግሞ ቁሳቁሶችን ለማዘጋጀት እና ለያንዳንዱ የተማሪ ቡድን የስራ ቦታዎችን ለማዘጋጀት ብዙ ጊዜ እና ጥረት ይጠይቃል፡፡ ተማሪዎች ሁል ጊዜ እዲሳተፉ ያደርጋል፡፡*

**ተማሪ ተኮር ዘዴ (student-cented approach)፡፡**

ተማሪን ያማከለ የመማሪያ ክፍሎች ተማሪዎችን በእቅድ ፣ ትግበራ እና ግምገማ ውስጥ ያካትታሉ፡፡ እንዲሁም መምህራን የአመራር ዘይቤያቸውን ከመመሪያ ወደ አማካሪነት በመቀየር ምቾት ይሰማቸዋል፡፡

**ፕሮጀክት ላይ የተመሰረት የትምህርት ፍሬም (project-based learning)፡፡**

በአንጻራዊነት አዲስ የማስተማር ዘዴ ፕሮጀክትን መሰረት ያደረገ ትምህርት ተማሪን የማከለ አካሄድ ነው፡፡

**ሞንቶሶሪ (Montessori)፡፡**

ይህ አይነቱ ትምህርት ከመቶ አመት በላይ በሆነ ዘዴ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ሆኖም ተማሪን ያማከለ የመማሪያ ክፍል ለመፍጠር አዲስ አቀራረብ መስጠቱን ቀጥሏል፡፡

**በጥያቄ ላይ የተመሰረተ የትምህርት ፍሬም (inquiry-based learning)፡፡**

በአሰሳ እና በከፍተኛ ደረጃ በመጠየቅ የእውነተኛ አለም ግንኙነቶችን በማድረግ ተማሪዎችን ያሳትፋል፡፡አስተማሪዎች ተማሪዎችን ሂሳዊ አስተሳሰብ እና ችግር የመፍታት ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ ይመራሉ፡፡

**የተገለበጠ የክላስ ክፍል ፍሬም (flipped classroom)፡፡**

ተማሪዎች ከቤት ወደ ክፍል ውስጥ ለመተካት የሚያዩዋቸውን የመስመር ላይ ትምህርቶችን የማቅረብ ጽንሰ ሀሳብ የተገለበጠ ትምህርት በመባል ይታወቃል፡፡ይህ ዘዴ በንድፈ ሀሳብ ከማስተማር ይልቅ በንቃት ለመማር በክፍል ውስጥ ብዙ ጊዜ እንዲኖር ያስችላል፡፡ ተማሪን ያማከለ ትምህርት እና ትብብርን ያበረታታል፡፡ ለመተግበር አስቸጋሪ ነው፡፡

**የትብብር መማሪያ ፍሬም (coopretive learning)፡፡**

ብዙ የቡድን ስራን በተቻለ መጠን ውጤታማ ለማድረግ ከመምህሩ በኩል ብዙ መዋቅር እና ጣልቃ ገብነት ይጠይቃል፡፡ በትብብር ስራ የማህበራዊ ክህሎቶችን ያሻሽላል የሚፈለግባቸውን የገሀዱ አለም የስራ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡በቡድን አባላት መካከል መሀበራዊ ሚናዎችን በማከፋፈል እና በዚህም ምክንያት አንድ ተማሪ ከቡድኑ መገለል ላይ ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

**ግላዊ ትምህርት (personalized education)፡፡**

በተቻለ መጠን ለያንዳንዱ ተማሪ ልዩ ፍላጎቶች ፣ ጥንካሬዎች እና ድክመቶች ምላሽ በመስጠት ተማሪን ያማከለ አካሄድን ወደ አዲስ ደረጃ ይወስዳል፡፡ጊዜና አደረጃጀት የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል፣ አስተማሪዎች ፍጥነታቸውን ማስተካከል፣ ብዙ ዝግጅት ማድረግ እና እያንደንዱን ተማሪ ፍላጎት መረዳትና ማሟላት ይጠይቃል (https://happynumbers.com/blog/list-of-teaching-methodologies-primary-school/)፡፡

**ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ (goal- oriented teaching method)፡፡**

አዲስ የዳበረ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ እድገቱ በሂደት ላይ የተመሰረተ ትምህርትና ማስተማር ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ግብ ተኮር ትምህርት በሶስት ዋና ዋና ደረጃዎች የተዋቀረ ነው፡፡

ሀ. ጽንሰ ሀሳቦችን ለመገንባት እና ለማገናኘት ምልከታ እና መግለጫ (observation and description to build ad connect concepts) ፤ለ. ጽብረቃ (reflection) እና  ሐ. በምክንያታዊነት ግብ ማውጣት (setting a goal with reasining) ናቸው፡፡

እንደ ርእሰ ጉዳዮች ይህ ተጨማሪ እርምጃዎችን በመጨመር ወይም ደረጃዎቹን በመድገም ሊራዘም ይችላል፡፡ለምሳሌ ራስን በመመልከት እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን በመመልከት ምልከታውን የበለጠ ሊከፋፈል ይችላል፡፡

ጽንሰ ሀሳብ ከተፈጠረ በኋላ ፣ ጽንሰ ሀሳቦቹ ትልልቅ ጽንሰ ሀሳቦችን ለመስራት አንድ ላይ ሊገናኙ ይችላሉ፡፡ መጀመሪያ ላይ ጽንሰ ሀሳቦችን ለመፍጠር እና ለማገናኘት በአንድ ወይም በሁለት እውቀት ሊጀምሩ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን አስተማሪዎች ከማስተማሪያ ቁሳቁሶች አዲስ እውቀት በመጨመር የጽንሰ ሀሳብ  እና የጽንሰ ሀሳብ ግንኙነት  ማስፋት ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች ገና ከጅምሩ ከፍተኛ መጠን ያለው እንዲያካሂዱ ቢጠይቁ በጣም ይገርማሉ፡፡ ስለዚህ በጣም ውጤታማው መንገድ በትንሹ መጀመር እንደ ክር መስራት አንድ በአንድ ይጨምሩ፡፡ ጽንሰ ሀሳቦች በመድገም እና በማገናኘት፣ አስተማሪዎች ተማሪዎችን የበለጠ እውቀት እንዲጠቀሙ ሊመሯቸው ይችላሉ፡፡ በዚህ ሂደት ተማሪዎች የተገነቡ እና የተገናኙ ጽንሰ ሀሳቦች እንዲገልጹ ማድረግም አስፈላጊ ነው፡፡ መግለጫው አመክንዮዎቹ እንዲታዩ ጽንሰ ሀሳቦቹን በምስል ማሳየት ነው፡፡ ይህ ጽንሰ ሀሳቦቹ እንዴት እደተገነቡና የተገናኙትን ጽንሰ ሀሳቦች እንዲገለጹ ማድረግም አስፈላጊ ነው፡፡  ይህ ጽንሰ ሀሳቦቹ እንዴት እንደተገነቡና እነደተገናኙ እንዲመለከቱ የሚያደርግ ነው፡፡ ተማሪዎች ጽንሰ ሀሳቦችን ከምልከታ ጀምሮ በትንሹ ድጋፍ ቢሹ መገንባት እና ማጋናኘት ይችላሉ፡፡

ተማሪዎች ግቦችን ለማውጣት ደረጃ 1. የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት (እውቀትና ክህሎት)፡፡ ደረጃ 2. ተማሪዎች ምሳሌን እንዲመለከቱ ማድረግ (ተማሪዎች እንዲያነቡ ጠይቅ፣ ቪዲዮዎችን ወይም ሌሎች የቀረቡ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ይመልከቱ)፡፡ ደረጃ 3. ተማሪዎች ምልከታቸውን እንዲገልጹ ጠይቋቸው (ይህ የእውቀት ጽንሰ ሀሳብ ሂደት ነው)፡፡  ደረጃ 4. ተማሪዎች ከደረጃ ሶስት ጽንሰ ሀሳቦችን እዲያገናኙ ይጠይቁ እና ይግለጹ፡፡ ደረጃ 5. ከደረጃ አራት ማብራሪያውን በማንጸባረቅ ተማሪዎች ጥያቄዎችን እንዲያቀርቡ ይጠይቋቸው፡፡ ደረጃ 6. ከደረጃ አምስት ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ተማሪዎች ግቦችን እንዲያወጡና ጥናታቸውን እንዲነድፉ ጠይቅ፡፡

ነገር  ግን  እውቀትን እና ክህሎቶችን ከማቅረብ በተቃራኒ እያንዳንዱን እርምጃ ማከናወን ያለባቸው ተማሪዎች መሆን አለባቸው፡፡ የአስተማሪዎች ሚና የተማሪዎችን ግብአቶች (እውቀት እና ክህሎቶች ለተማሪዎች እንዲጠቀሙበት) እና መመሪያ መስጥት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ አውቀት እና ችሎታዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ ግን ዋና ትኩረት አይደሉም፡፡ ዋናው ትኩረት በእውቀትና በክህሎት ግብን የማውጣት ሂደት ነው፡፡ ይህ ከፕሮጀክት- ተኮር ትምህርት ጋር መምታታት የለበትም፡፡

አስተማሪዎች ተማሪዎቸሪዎች እንዲያከናውኑ ፕሮጀክት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ግቡን ያማከለ የማስተማር ዘዴ ተማሪዎች ከጥናት በፊት ያለውን ግብ በራሳቸው የማውጣት ችሎታ እንዲያዳብሩ ነው፡፡

ከግብ ተኮር የማስተማር ሂደት ውስጥ በጣም ፈታኙ እርምጃ ግብ ለማውጣት ጥያቄዎችን መፍጠር ነው፡፡ምክንያቱም አብዛኛው ተማሪዎች በእውቀት እና በክህሎት ላይ የተመሰረተ ትምህርት ስላለፈ እና ይህም ተማሪዎችን እንዳይጠይቁ ስለሚያደርግ ነው፡፡ በእውቀትና በክህሎት ላይ ያተኮረ ትምህርት ተማሪዎችን በእውቀት ወይም በክህሎት ትክክለኛነት ይገመግማል፡፡ ግምገማው ትክክለኛ መልሶች ላይ ያተኮረ ሲሆን ተማሪዎች በተለይ ጥያቄው ትክክለኛው ጥያቄ ስለመሆኑ ሲጠራጠሩ ጥያቄዎችን መጠየቅ አይችሉም፡፡ ግብ ለማውጣት ጥያቄዎች መሆን አለባቸው ምክንያቱም ግብ ማለት ያልተገለጸ ወይም ገና ያልተገኘ ማለት ነው ( international journal for infonomics(IJI), volume 13, issue 2, 2020)፡፡

## 2.1.7 የጽህፈት ክሂል ምዘና

እስካሁን የጽህፈት ችሎታን ለመመዘን ሁለት መሰረታዊ ዘዴዎች (approach) ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ እነሱም ኢርቱእ (indirect) እና ርቱእ (direct) የጽህፈት ምዘና ዘዴዎች በመባል ይታወቃሉ (Weir; 2005; Coombe et al 2007)፡፡

### 2.1.7.1 ኢርቱእ (indirect) የጽህፈት ምዘና

ኢርቱእ (indirect) የምዘና ዘዴ አንዳንድ ጊዜ ምርጫ ነክ ምዘና ተብሎ ይጠራል ፡፡ ተፈታኙን እንዲጽፍ የሚጠይቅ ሳይሆን ፤ በምረጫ ነክ ለቀረቡልት ጥያቄዎች ምላሽ እዲሰጥ ብቻ የሚጠይቅ ነው (Stiggins, 1982) ፡፡ ኢርቱእ (indirect) ምዘና ስለውጤታማ ጽህፈት ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን ያጠቃቀም ስርአቶች እንደ ሰዋስው፣ ስርአተ ነጥብ፣ አረፍተነገር ምስረታ፣ አወቃቀርና ሌሎችን አጠቃቀሞችን የተገነዘቡ መሆናቸውን የሚመዝን መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ይህ ዘዴ በሌላ መልኩ የአንድን ተማሪ የጽህፈት ችሎታ ለመገምገም የሚያስችል አስፈላጊ ግን ደግሞ በቂ ያልሆነ መረጃ ይሰጣል፡፡

በኢርቱእ (indirect) የምዘና ዘዴዎች ተማሪዎቸ የመጻፍ ስራን ወይም የመድረስ ሂደትእዲያከናውኑ አይጠየቁም ፡፡ በሌላ አገላለጽ በእንደዚህ አይነት ምዘናዎች የቋንቋ ህጎችና የአጻጻፍ ስርአቶች ይመዘናሉ፡፡ እንደ Heaton (1988) ገለጻ በቃል መጻፍን ፣ ቃላትን አስተካክሎ መጻፍና ተገቢ ቃላትን መርጦ የመጠቀም ችሎታን የሚጠይቁ በምርጫ መልክ ጥያቄዎችን ፣ጅምር አረፍተ ነገሮችን ማሟላትን ፣ ወዘተ በኢርቱእ (indirect) ምዘና አይነት ውስጥ በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እንደዚህ አይነት ጥያቄዎች ተጨባጭነት ባለው ፣ ፈጣንና አስተማማኝነት ባለው ሁኔታ ለማረም ምቹ ናቸው፡፡ Tribbe (1996) በተመሳሳይ ሁኔታ ኢርቱእ (indirect) የጽህፈት ምዘና በምርጫና በዝግ የፈተና አይነቶች አማካኝነት አንድ ተፈታኝ በአረፍተ ነገር ደረጃ የአረፍተ ነገሮችን ሰዋስዋዊ ስህተቶች፣ የፊደልና የስርአተ ነጥብ ጉድለቶችን እንዲያስተካክሉ የሚጠይቅ ነው በማለት ገልጸውታል፡፡

በኢርቱእ (indirect) ምዘና ላይ የሚነሱት ችግሮች ውስጥ አንዱ ጸሀፊዎች ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን እንዴት መመስረት እንደ ሚችሉ መረጃ መስጠት አዳጋች መሆኑ ነው (Weir, 2005) ፡፡ ሁለተኛውና በተደጋጋሚ በኢርቱእ ምዘና ላይ ሚሰነዘረው ትችት ፣ አሉታዊ ተጽእኖ ማስከተሉ ነው፡፡ ተማሪዎች እንዲያዳብሩ የሚፈለገው ትክክለኛ ክንውን እዲለማመዱ እድል አይሰጥም (Bailey, 1998) ፡፡ ሶስተኛ ከባድ ትችት በኢርቱእ የጽህፈት ምዘና ላይ የደረሰው ከአግባብነት አኳያ ሲታይ

ነው፡፤ ሁሉም ተመራማሪዎች ርቱእ እና ኢ-ርቱእ ምዘናዎች ብዙውን ጊዜ አንድም በከፍተኛ አልያም በመካከለኛ ሁኔታ እንደሚዛመዱ የተለያዩ ስራዎች አሳይተዋል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ግኝቶች ኢ-ርቱእ ምዘና በተሟላ ሁኔታ የጽህፈት ችሎታን የሳያል አላሉም፡፡ ለዚህም ደግሞ ምክንያቱ ኢ-ርቱእ ምዘናዎች የጽህፈት ችሎታን በትክክል ማሰየት አለመቻላቸው ነው፡፡ ከዚያ ይልቅ ሁለቱን በጥምረት መጠቀምና የሚይዙትንም የውጤት መጠን ማሳወቅ የሚሻል እንደሆነ ይመከራል፡፡ ይሁን እንጂ በአንድ ፈተና ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸው የኢ-ርቱ እና የርቱእ ጥያቄዎች መጠን ግን እስካሁንም ድረስ ለክርክር ክፍት ነው (Koffler, 1984 )፡፡

## 2.1.7.2 ርቱእ (direct) የጽህፈት ምዘና


ርቱእ የጽፈት ምዘና ዘዴ የተማሪዎችን የጽፈት ችሎታ በጻፏቸው ጽሁፎች አማካኝነት መመዘኑ ላይ ያነጣጥራል ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እዲህ አይነቱ ምዘና ተማሪዎች መረጃን እዲተነትኑ ፣ እዲያጠቃልሉ፣ በአዲስ መልክ እዲያደራጁና እዲገመግሙ እድል የሚሰጥ በመሆኑ ተመራጭነት እያገኘ ነው፡፡ በአሁን ጊዜ ርቱእ የጽፈት ምዘናዎች ከኢ-ርቱእ  የጽፈት ምዘናዎች በተሻለ ሁኔታ የተማሪዎችን የጽህፈት ችሎታ ስለሚለኩ በብዙ የትምህርት ተቋምት ተመራጭ እየሆኑ መጥተዋል ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች የራሳቸውን ጹሁፍ አንዲያሻሽሉ ያበረታታሉ ከዚህም በላይ ርቱእ ምዘናዎች እውናዊ (Authentic) በመሆናቸው ጠቃሚ ናቸው፤ ምክንያቱም አብዛኞቹ ተግባራት የገሀዱን አለም የሚወክሉ ናቸው፡፡ ርቱእ የጽህፈት ምዘናዎች ሁሉም የጽህፈት አለባዉያን አዋህደው የሚይዙ ናቸው፡፡ ስለሆነም በርቱእ የጽህፈት ምዘና አማካኝነት አንድ ጻሀፊ ምን ያህል ጥሩ ጻፊ ወይም በጽሁፍ አማካኝነት ምን ሊያከናውን እነደሚችል መግለጽ ይቻላል (Weir, 1993) ፡፡

ርቱእ የጽህፈት ምዘናዎች በሁለት አይነት መንግድ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ነጻ ጽህፈት (free writing) እና ግድብ ጽህፈት (control writng) ተግባራት ናቸው (Weir, 1990 ፤ Weir, 1993 ፤ Coomble et al , 2007)፡፡ ነጻ የጽህፈት ተግባር ተፈታኞቹ የቀረበውን ጥያቄ ያነቡና ዳራዊ እውቀታቸውንና ከኮርሱ የተማሩትን እውቀት በምጣመር የታቀደ ምላሽ እንዲሰጡ ይጠይቃል፡፡ ግድብ ጽህፈት (control writng) ተግባር ደግሞ በጥያቄው ውስጥ የቀረበውን ይዘት (በአብዛኛው በቻርት ወይም በዲያግራም መላክ የሚቀርቡ መረጃዎችን ) በመጠቀም አንዲጽፉ የሚጠይቅ ነው (Soombe et al ; 2007)፡፡

ኢ-ርቱእ ምዘና ከፍተኛ አስተማማኝነት ያለው ፣ ለመፈተንና ለማረም የሚቀል ሲሆን ፣ ርቱእ የምዘና ስልት ደግሞ ከፍትኛ አግባብንት ያለው እውናዊ ተግባቦትን የሚያንጸባርቅ ፣ የጽህፍት ችሎታን በቀጥታ የሚለካ ፣ ሁሉንም የጽህፈት አላባዎች አቀናጅቶ የሚይዝ ነው ከበለጠ ያእቆብ (2006) የተወሰደ፡፡

## 2.2.ጥናቱ የሚከተለው የንድፍ ሀሳብ ማእቀፍ

ይህ ጥናት በዋነነት ትኩረት የሚያደርግባቸው ነጻ እና ጥገኛ ተለዋዋጮቸ ያላቸውን የእረስ በርስ ዝምድና የሚያሳይ እና የጥናቱ አካሄድ የሚያሳይ አጠቃቀም ጽንሰ ሀሳባዊ መአቀፍ መግለጫ ነዉ፡፡



ከላይ የቀረበው ስእላዊ በግለጫ የሚያመለክተው የቋንቋ ትምህርት ከሚሰጥባቸው አላማዎች አንዱ ክሂሎችን ለማዳበር ሲሆን ከአራቱ ክሂሎች ውስጥ አንዱ ደግሞ የመጻፍ ክሂል ነው፡፡ ይህን የመጻፍ ክሂል ደግሞ ለማስተማር የተለያዩ ዘዴዎችን እነጠቀማለን፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት አላማ ግብ ተኮር የማስተማር ዘዴን ተጠቅሞ የመጻፍ ክሂልን ማስተማር ያለው ሚና የሚፈተሽ ሲሆን የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኖች በቅድመ እና በድህረ ፈተና የሚያመጡት ውጤት መኖሩን ከዚህ በላይ በተቀመጡት ሳጥኖች የእርስ በእርስ ግንኙነታቸውን እንረዳለን፡፡ ጥናቱ የሚከተለው ንድፍ ከፊል ፍትነታዊ በመሆኑ የተማሪዎች ቅድመ እና ድህረ ፈተና ውጤት እነለይበታለን፡፡

## 2.3.የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

የጽፈት ትምህርትን በተመለከተ በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከዚህ ጥናት ጋር ሊቃረብ ይችላል ተብሎ የታሰበው ጥናት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ በማሬ (2011) ችግር ፈቺ የማሰተማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ያለው አስተዋጽኦ በዘጠነኛ ክፈል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ከፊል ሙከራዊ ጥናት በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የድህረ መረቃ ማሚያ ጥናት አካሂዳለች፡፡ አጥኝዋ ባለሁለት ቡድን ከፊል ሙከራዊ ንድፍ ተግባር ላይ አውላለች፡፡ ይህ ጥናት የተካሄደበት ቦታ ጎንደር ከተማ አስተዳደር ሲሆን ቦታው በአመቺ ናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጧል፡፡መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተጠቀመችበት ስልት ፈተና ነው፡፡መረጃዎች የተተነተኑበት ስልት በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት ነው፡፡የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በቅደመ የመጻፍ ክሂል በቡድኖቹ መካከል ጉልህ ልዩነት እንዳልታየ የተገኘው ውጤት አመላክቷል፡፡በድህረ ፈተና ውጤት ደግሞ የተሻለ ልዩነት አምጥቷል፡፡ ስለዚህ ችግር ፈቺ የማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂልን ለማሻሻል አስተዋጽኦ አለው፡፡

በላይነህ( 2000) የጥናቱ ዋና አላማ ሂደታዊ የአጻጻፍ ብልሃት በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂልን ለማጎልበት ያለዉን ሚና መመርመር የሚል ሲሆን የጥናቱ ዉጤትም በሂደታዊ የአጻጻፍ ብልሃት ተደጋጋሚ ረቂቆችና የመጻፍ ክሂልን እንደሚያጎለብት ያሳያል፡፡

ይህ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለዉ በመጻፍ ክሂል ላይ እና በሂደታዊ የማስተማር ዘዴ ላይ ያተኮረ መሆኑ ሲሆን ነገር ግን የተገለጸዉ ጥናት የተከናወነበት ጊዜና ቦታ የተለየ ከሆኑ በላይ ሂደታዊ የማስተማር ዘዴ የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ከማሻሻል አንጻር ላይ ብቻ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት ሂደታዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለዉን ሚና የሚመረምር መሆኑ ከዚህ ጥናት ይለየዋል፡፡

እስከ አሁን አጥኝዋ ባደረገችው ዳሰሳ ግብ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ተጠቅሞ ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ያለው ሚና በሚል ጥናት ስላልተካሄደ አጥኚዋ ግብ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂልን ለማሻሻል ያለው ሚና በሚል ከፊል ሙከራዊ ጥናት በአማርኛ ቋንቋ ለመለየት ይህን ጥናት አካይዳለች፡፡

## ም ዕራፍ ሶስት

# የጥናቱ ንድፍና የአጠናን ዘዴ

### 3.1.የጥናቱ ንድፍ

በምእራፍ አንድ ለመግለጽ እንደተሞከረው የዚህ ጥናት አላማ ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ተጠቅሞ ማስተማር የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ያለው ሚና በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት መለየት ነው፡፡ ለዚህም የተመረጠው የአጠናን ዘዴ መጠናዊ የምርምር ዘዴ (quantitative method) ሲሆን አቀራረቡ ደግሞ ከፊል ፍትነታዊ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ መረጃዎችን ማሰባሰቢያ ዘዴ ቅድመ እና ድህረ   ፈተና ነው፡፡ የሚያስፈልጉ ተጠኚዎች በሚከተሉት ስልቶች ተመርጠዋል፡፡

### 3.2. የጥናቱ አካላይ

ጥናቱ በአመቺ ንሞና ዘዴ በተመረጠዉ በኦሮሚያ ክልል በኢሉባቦር ዞን በዳሪሙ ወረዳ ዳሪሙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ አተኩሯል፡፡ አጥኚዋ በኢሉባቦር ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች ዉስጥ ዳሪሙ ወረዳ ዳሪሙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን በአመቺ ናሙና የመረጠችበት ምክንያት የአጥኝዋ የስራ ቦታ በመሆኑ የተነሳ ነዉ፡፡

### 3.3. የናሙናዎች አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የተመረጠው ትምህርት ቤት በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በኢሉባቦር ዞን በዳሪሙ ወረዳ የሚገኘው የዳሪሙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ የተመረጠው በአመቺ ናሙና  ስልት ነው፡፡ ይህ ትምህርት ቤት የተመረጠበት ምክንያት አጥኚዋ በዚህ ትምህርት ቤት በመምህርነት ሙያ ስለምታገለግል ጥናቱ ከፊል ሙከራዊ በመሆኑ የተነሳ ከአንድ ትምህርት ቤት በላይ ተዘዋውሮ ለመስራት የማያስችል በመሆኑ ነው፡፡

## 3.3.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ

አጥኝዋ ለጥናቱ በአመቺ የንሞና ዘዴ በመጠቀም የዳሪሙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን መርጣለች፡፡ ይህም የተደረገበት ምክንያት ትምህርት ቤቱ የአጥኝዋ የስራ ቦታ በመሆኑ የሙከራ ትምህርቱንና አጠቃላይ የጥናቱን ሂደት በቅርበት ለመከታተልና ለማከናወን እንዲያመቻት በማሰብ ነዉ፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ ሙከራዊ በመሆኑ የዕለት ከዕለት ክትትልና ግምገማ ስለሚያስፈልገዉ በቅርበት መሆኑ የተሻለ ነዉ ብላ በማሰብ ነዉ፡፡

## 3.3.2. የክፍል ደረጃ አመራረጥ እና የተጠኚዎች ናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት የተካተቱት ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ዉስጥ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸዉ፡፡ በትምህርት ቤቱ ከሚገኙት ተማሪዎች የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የተመረጡበት በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ነዉ፡፡ ይህ ክፍል ደረጃ የተመረጠበት ምክንያት በመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚመጡት በዘጠነኛ ክፍል ሲሆን ለትምህርት ቤቱ አዲስ እንደመሆናቸዉ መጠን መረጃዉን በትክክል አይሰጡም ከሚል እሳቤ ነዉ፡፡ አስራ አንደኛና አስራ ሁለተኛ ክፍል ደግሞ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ስለማይማሩነዉ፡፡ የተማሪዎች የክፍል ደረጃ ከተመረጠ በኋላ በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ አምስት የአስረኛ ክፍል ምድቦች ዉስጥ ሁለቱ በቀላል የእጣ ንሞና ተመርጠዋል፡፡ በዚህም መሰረት አስረኛ"C"ምድብ የመማሪያ ክፍል እና አስረኛ"E" ምድብ የመማሪያ ክፍል ተካትቷዋል፡፡ ተማሪዎች ከተመረጡ

በኋላ በሁለቱ ምድቦች ዉስጥ የተካተቱት ተማሪዎች ተመጣጣኝ የመጻፍ ችሎታ እንዳላቸዉ ለማረጋገጥ በክፍል ዉስጥ ለመለያ በተዘጋጀ ፈተና አማካኝነት 100% በመዉሰድ የ "C"ምድብ አማካይ ዉጤት 53.7778 ሲሆን የ "E" ምድብ ደግሞ 50.2571 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ የተመዘገበውን ውጤት ልዩነት በባእድ ቲ-ቴስት የተፈተሸ ሲሆን የተገኘው የቲ-ቴስት ውጤት -1.539 እና የጉልህነት ውጤት መፈተሻ የ (significant level) 0.024 በመሆን ልዩነቱ ጉልህ እንዳልሆነ አሳይቷል፡፡

የፈተና ይዘትም ትኩረት ያደረገው በመጻፍ ክሂል ተግባር ላይ ሲሆን የእርማት ሂደቱም የተከናወነው በሚያስተምሩ መምህራን ነው፡፡ ይህም ሰፊ የሆነ ልዩነት ባለማምጣቱ ተቀራራቢ እንደሆነ በማረጋገጥ የተመረጠ ነው፡፡ ተመጣጣኝነቱ ከተረጋገጠ በኋላ እጣ በማውጣት አስረኛ "C" ን በሙከራ ቡድን ፣ "E"ን ደግሞ በቁጥጥር ቡድን በመመደብ የሙከራ ትምህርቱ ተከናውኗል፡፡ በእያንዳንዱ ምድብ ማለትም ከ"C" ወንድ 29 ሴት 23 በድምሩ 52 ተማሪዎች በሁለተኛው ምድብ ማለትም በ"E" ደግሞ ወንድ 24 ሴት 20 ድምር 44 ተማሪዎች ሲመረጡ ከሁለቱም ምድቦች በአተቃላይ ወንድ 53 ሴት 43 በድምሩ በሁለቱ ምድቦች ተማሪዎች የጥናቱ ተተኳሪ ሆነዋል፡፡ ነገር ግን መረጃው በሚሰበሰብበት ወቅት ከተመረጡት ሁለት ምድቦች ማለትም (ከቁጥጥር ቡድን 25 ፣ ከሙከራ ቡድን 9 ተማሪ) በአጠቃላይ 34 ተማሪዎች በግል ጉዳይ ምክንያት ሊገኙ ባለመቻላቸው መረጃው ከ62 ተማሪዎች (ወንድ 32 ፣ ሴት 30) እጣ በማውጣት "C" ን (27 ተማሪዎች ) በሙከራ ቡድን ፣ አስረኛ "E"ን (35 ተማሪዎች) ደግሞ በቁጥጥር ቡድን በመመደብ የሙከራ ትምህርቱ ተከናውኗል፡፡

## 3.4 የትምህርት ይዘት አመራረጥ

ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና ለመመርመር የሙከራ ትምህርት እንደሚከናውን ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ የሙከራ ትምህርቱም ለስድስት ሳምንታት ( ለአስራሁለት ክፍለ ጊዜዎች) የተከናወነ ሲሆን ለአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ስድስት የመጻፍ ትምህርት ይዘቶች ተመርጠዋል፡፡ ይዘቶቹ የተመረጡት በአላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ሲሆን ይህም የተደረገበት ምክንያት ይዘቶቹ ለግብ ተኮር ዘዴ አመች የሆኑ እና ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ ለማድረግ ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

ይህንን ለማድረግም በመማሪያ መጽሐፍ የሚገኙት የመጻፍ ትምህርት ይዘቶችና መለማመጃዎች በመርሀ ትምህርቱ መሰረት በሁለተኛ ወሰነ ትምህርት ከተካተቱት አምስት ምዕራፎች ላይ ትኩረት ያደረገ ነዉ፡፡ በተደጋጋሚ ከቀረቡ የመጻፍ ተግባራት ዉስጥ ምዕራፍ አስር ለተግባሩ በመምረጥ ለሁለቱ ቡድኖች በተመሳሳይ ይዘት በተለያየ የማስተማርያ ዘዴ በመጠቀም ተከናዉኗል፡፡

## 3.5 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

የጥናቱን መሰረታዊ መላምት ለመመለስ ይቻል ዘንድ አስፈላጊውን መረጃ መሰብሰብ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ተግባር ይረዳ ዘንድ በዚህ ጥናት ውስጥ መረጃ ለመሰብሰብ አጥኝዋ የምትጠቀመው ፈተና ነው፡፡ ለዚህም የቁጥጥርና የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ትምህርቱ ከመሰጠቱ በፊት የመጻፍ ክሂላቸው ተቀራራቢ መሆን አለመሆኑን ለመለየት የቅድመ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷል፡፡ በመቀጠል ለሁለቱም ቡድን ተማሪዎች በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች ከተማሩ በኃላ ከመጻፍ ክሂል አንጻር ሊመጣ የሚችለውን ለውጥ ለማረጋገጥ ደግሞ የድህረ ትምህርት ፈተና በአጥኝዋ ተፈትነዋል፡፡ በዚህ መሰረት ከፈተና የተገኙት መረጃዎች በግብ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ በተማሪዎች የመጻፍ ሎታ ላይ ያሰገኘውን ሚና ለመለካት ያገለግላል፡፡

## 3.6 ፈተና

የዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ ያገለገለው ፈተና ነው፡፡ የተሰጠው ሁለት ጊዜ ሲሆን ሁለት አማዎችም አሉት፡፡ መጀመሪያ የሚሰጠው ቅድመ ፈተና ሲሆን የሙከራ ትምህርቱ ከመከናወኑ በፊት ለሁለቱም ቡድኖች ይሰጣል፡፡ የዚህ ፈተና ዋነኛ አላማውም የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ተመጣጣኝ የመጻፍ ችሎታ መኖር አለመኖሩን ለመለየት፡፡ ሁለተኛ የተሰጠው ፈተና ደግሞ ድህረ ፈተና ሲሆን የሙከራ ትምህርቱ ለአስራ ሁለት ክፍለ ጊዜዎች ከተሰጠ በኋላ ለሁለቱም ቡድኖች በተመሳሳይ ሰዓትና የመፈተኛ ክፍል ተሰጥቷል፡፡ የዚህ ፈተና ዋነኛ አላማም ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ በሙከራ ቡድን ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ ያሳደረውን አንድምታ መገምገም ነው፡፡ ቅድመ ፈተናውና ድህረ ፈተናው ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ሲሆን ለቅድመ ፈተናው አንድ ጥያቄ የቀረበ ሲሆን ለድህረ ፈተናውም አንድ ጥያቄ በማዘጋጀት ተከናውኗል፡፡

ፈተናዎቹም የተዘጋጁት በተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ ላይ ለመጻፍ ተግባር ከተሰጡት ውስጥ በተደጋጋሚ ከሚሰጣቸው ተግባር በብዛት ትኩረት ተደረገባቸው ምእራፍ አስር ሲሆን ተማሪዎች ለትምህርት ቤታቸው የሸኚ ደብዳቤ እዲሰጣቸው ማመልከቻ እንዲጽፉ ተደርጓል፡፡

## 3.7 የመረጃ አተናተን

በዚህ ጥናት ዉስጥ ጥቅም ላይ የዋለዉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ፈተና ሲሆን የተገኙ መረጃዎች የተተነተኑት እንደሚከተለዉ ነዉ፡፡ የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኑ በቅድመ እና በድህረ የመጻፍ ክሂል ፈተና ቡድን ለቡድን ለማነጻጸር በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ እንዲሁም እያንዳንዱ ቡድን በቅድመ እና በድህረ የመጻፍ ክሂል ፈተና ያስመዘገቧቸዉን ዉጤቶች በተናጥል ለመፈተሽ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

## 4.1. የጥናቱ ውጤት ትንተና

የዚህ ጥናት መሰረታዊ ጥያቄ ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ሚና አለውን? የሚል ሲሆን መላምቱ ደግሞ ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ሚና አለው፡፡ የሚል ነው፡፡ጥያቄውን ለመመለስና መላምቱን ለመፈተሽ መረጃዎች በባእድና በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል፡፡

ምዘናው የተከናወነው በርቱእ የጽህፈት ምዘና ዘዴ ነው፡፡ርቱእ የጽፈት ምዘና ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ በጻፏቸው ጽሁፎች አማካኝነት መመዘኑ ላይ ያነጣጥራል ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እዲህ አይነቱ ምዘና ተማሪዎች መረጃን እዲተነትኑ ፣ እዲያጠቃልሉ፣ በአዲስ መልክ እዲያደራጁና እዲገመግሙ እድል የሚሰጥ በመሆኑ ተመራጭነት እያገኘ ነው፡፡ በአሁን ጊዜ ርቱእ የጽፈት ምዘናዎች ከኢርቱእ  የጽፈት ምዘናዎች በተሻለ ሁኔታ የተማሪዎችን የጽህፈት ችሎታ ስለሚለኩ በብዙ የትምህርት ተቋምት ተመራጭ እየሆኑ መጥተዋል ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች የራሳቸውን ጹሁፍ እንዲያሻሽሉ ያበረታታሉ ከዚህም በላይ ርቱእ ምዘናዎች እውናዊ (Authentic) በመሆናቸው ጠቃሚ ናቸው፤ ምክንያቱም አብዛኞቹ ተግባራት የገሀዱን አለም የሚወክሉ ናቸው፡፡ ርቱእ የጽህፈት ምዘናዎች ሁሉም የጽህፈት አለባዉያን አዋህደው የሚይዙ ናቸው፡፡ ስለሆነም በርቱእ የጽህፈት ምዘና አማካኝነት አንድ ጸሀፊ ምን ያህል ጥሩ ጻፊ ወይም በጽሁፍ አማካኝነት ምን ሊያከናውን እነደሚችል መግለጽ ይቻላል (Weir, 1993) ፡፡

የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ከሙከራ በፊት ያላቸው የመጻፍ ክሂል ችሎታ ተቀራራቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር በባእድና በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል፡፡ የተገኘው ውጤትም ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.1፡- የተተኳሪ ቡድኖች ቅድመ ፈተና ውጤት ንጽጽር /በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት/**

| ምድብ | የናሙና ብዛት | አማካይ | መደበኛ ልይይት | የቲ ዋጋ T | የነጻነት ደረጃ (DF) | የጉልህነት ውጤት (sig) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 27 | 53.7778 | 10.23412 | -1.539 | 60 | 0.024 |
| የቁጥጥር ቡድን | 35 | 50.2571 | 7.78514 | | | |

ከላይ በሰንጠረዡ ያለው መረጃ የሚያሳየው የቅድመ ፈተናውን የተፈተኑ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ አማካይ ውጤት (53.7778) ፣ ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ አማካይ ውጤት (50.2571) በ (3.5207) የበለጠ መሆኑን ያመለክታል፡፡ እንዲሁም የሙከራ ቡድኑ የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና መደበኛ ልይይት

(10.23412) ፣ ከቁጥጥር ቡድኑ የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና መደበኛ ልይይት (7.78514) በ (2.44898) ልዩነት አምጥቷል፡፡

ከቀረበው ትንተና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ አማካይ ውጤት እንደበለጠ ለማየት ተችሏል፡፡

በመካከላቸው ያለው የጉልህነት ደረጃ ሲታይ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት እንደሌላቸው በ 60 የነጻነት ደረጃ ቲ (-1.539) =2.00 ፣ የጉልህነት ውጤት (sig=0.024) ከ0.05 በታች ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በሁለቱ ቡድኖች ቅድመ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካዮች መካከል የጎላ ልዩት አለመኖሩን አመልክቷል፡፡ ይህም በሁለቱ ተተኳሪ ቡድኖች መካከል ተቀራራቢ የመጻፍ ክሂል ችሎታ መኖሩን ስለሚያሳይ ሙከራው በቡድኖቹ ላይ እንዲቀጥል ሆኗል፡፡

ከዚህ በመቀጠል የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂልን ለስድስት ሳምንታት ያክል እንዲማሩ ከተደረገ በኃላ ቡድኖቹ ያመጡትን ለውጥ ለመመርመር ድህረ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷል፣ ውጤቱ በባእድና በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ዘዴ ተሰልቷል፡፡ ከዚህ በታች የቀረበው ሰንጠረዥም የተገኘውን ውጤት አሳይቷል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.2፡- የተተኳሪ ቡድኖች ድህረ የመጻፍ ክሂል ውጤት ንጽጽር/ በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት/**

| ምድብ | የናሙና ብዛት | አማካይ | መደበኛ ልይይት | የቲ ዋጋ T | የነጻነትደረጃ (DF) | የጉልህነት ውጤት (sig) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 27 | 60.0926 | 15.37545 | -2.799 | 60 | 0.000 |
| የቁጥጥር ቡድን | 35 | 52.0000 | 6.64211 | | | |

ከድህረ ትምህርቱ የመጻፍ ክሂል ፈተና መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት (60.0926) ፣ ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት (52.0000) ልዩነቱ በ (8.0926) በልጦ ተሰልቷል፡፡ ሁለቱ ቡድኖች ያስመዘገቡት ውጤት ከአማካይ ውጤቱ በአማካይ ያለው ልዩነት ሲታይ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና መደበኛ ልይይት ውጤት (15.37545) ፣ ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና መደበኛ ልይይት ውጤት (6.64211) በ (8.733339) ልዩነት አሳይቷል፡፡

በመሆኑም በመካከላቸው ያለው ልዩነት ሲታይም፣ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት በ60 የነጻነት ደረጃ ቲ (-2.799) =2.00 ፣ የጉልህነት ውጤት (sig. = 0.000) ከ0.05 በታች ሆኖ ተግኝቷል፡፡ ይህም በሁለቱ ቡድኖች ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካዮች መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን አመልክቷል፡፡ ከላይ ባለው ሰንጠረዥ የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤቱ ክፍ ብሎ ስለታየ በቡድኖቹ መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል፡፡

በመሆኑም እያንዳንዱ ቡድን በቅድመና በድህረ ፈተና ያስመዘገቡትን ውጤት በተናጥል  በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ማነጻጸር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ በታች የቀረበው ሰንጠረዥም የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በቅድመና በድህረ የመጻፍ ክሂል ፈተና ያስመዘገቧቸው አማካዮች ሲነጻጸሩ የተገኘው ውጤት ስሌት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.3፡- የሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤት በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር**

| ፈተና | የተሳታፊዎች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነት ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ፈተና | 27 | 53.7778 | 10.23412 | -3.706 | 26 | 0.001 |
| ድህረ ፈተና | 27 | 60.0926 | 15.37545 | | | |

ከላይ ባለው ሰንጠረዥ እንደሚታየው የሙከራ ቡድኑ ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት (60.0926) ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (53.7778) በ6.3138 በልጦ ይታያል፡፡ የመደበኛ ልይይት ውጤት እንደሚያሳየውም የድህረ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት (15.37545) ከቅድመ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት (10.23412) በ5.14133 ልዩነት አሳይቷል፡፡

በመሆኑም በመካከላቸው ያለው ልዩነት ሲታይም ፣ የቅድመ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ከድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት እንዳላቸው በ26 የነጻነት ደረጃ ቲ (-3.706) = 2.06 ፣ የጉልህነት ውጤት (sig. = 0.001) ከ0.05 በታች ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን አመልክቷል፡፡

የጉልህ ልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃም ተሰልቶ ፣ (Cohen's d= 0.71315) መጥቷል፡፡ ይህ መካከለኛ ዝምድና ጥንካሬ ደረጃን የሚያሳይ ነው፡፡ የዝምድና ጥንካሬ ደረጃ የባለ ሁለት ጫፍ የsig. ዋጋ ከ0.05 በታች ከሆነ የሚሰላ ነው፡፡ የጉልህነት ውጤቱ ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ሲያመለክት ፣ Cohen's d (1988) ደግሞ ከsig. ዋጋው በመነሳት የጉልህነት ደረጃውን ያሳያል፡፡ በዚህ መሰረት ከ0 - 0.2 = ደካማ ፣ ከ0.21-0.5= መጠነኛ ፣  ከ0.51- 1=መካከለኛ እና ከ1 በላይ ጠንካራ የጉልህነት ደረጃን ያመለክታል፡፡

የትንተና ወጤቱም እንደሚያሳየው  የዝምድና ጥንካሬው መካከለኛ ቢሆንም ከድህረና ቅድመ የመጻፍ ክሂል ውጤት አንጻር ጉልህ ልዩነት እንዳላቸው ያሳል፡፡ ይህ ልዩነት የመጣው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በግብ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂልን በመማራቸው እንደሆነ ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተናዎች ያስመዘገቧቸው አማካዮች ጉልህ ልዩነት ማሳየት አለመቻላቸውን ለመፈተሽ ውጤቱ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ዘዴ ተሰልቷል፡፡ ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥም የተገኘውን ውጤት ያሳያል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.4፡- የቁጥጥር ቡድኑ ቀድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤት በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር**

| ፈተና | የተሳታፊዎች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነት ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ፈተና | 35 | 50.2571 | 7.78514 | -2.234 | 34 | 0.032 |
| ድህረ ፈተና | 35 | 52.0000 | 6.64211 | | | |

ከላይ እንደሚታየው የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት (52.0000) ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (50.2571) በ 1.7429 በልጦ ይታያል፡፡ የመደበኛ ልይይት ውጤት እነደሚያሳየውም የድህረ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት (6.64211) ከቅድመ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት (7.78514) በ 1.14303 ልዩነት አሳይቷል፡፡

በመካከላቸው ያለው ልዩነት ሲታይም ፣ ቅድመ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ከድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት እንደሌላቸው በ34 የነጻነት ደረጃ ቲ- (-2.234) = 2.04 የጉልህነት ውጤት 0.032 ከመቁረጫው ነጥብ 0.05 በታች መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከላይ እንደሚታየው በሙከራ ቡድኑ ከድህረ የመጻፍ ክሂል ውጤት አንጻር ጉልህ ልዩነት ሲታይ በቁጥጥር ቡድኑ ግን ጉልህ ልዩነት አልታየም፡፡ የውጤቱ ልዩነትም ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ በመተግበሩ ምክንያት የመጣ መሆኑን ሊጠቁም ይችላል፡፡

## 4.2.የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ትኩረት ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚና መመርመር ነው፡፡ ይህ አላማ በአቅጣጫ ጠቋሚ መላምት የተገለጸ ሲሆን የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ እና መላምቶችን ለመፈተሽ በቅድመ ትምህርት ፈተና እና ድህረ ትምህርት ፈተና መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

በግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለውጥ ማምጣት አለማምጣቱን ለማረጋገጥ የተሰበሰቡት መረጃዎች ሁለቱ ቡድኖች በቅድመና ድህረ የመጻፍ ክሂል ያስመዘገቧቸው ውጤቶች በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት እያንዳንዱን ቡድን በቅድመና ድህረ የመጻፍ ክሂል ያስመዘገቧቸው ውጤቶች በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና እንዲሰላ ተደርጓል፡፡

በጥናቱ ውጤት ትንተና በመጀመሪያ የተፈተሸው የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የቅድመ መጻፍ ክሂል ውጤት ነው፡፡ በመሆኑም ቅድመ የመጻፍ ክሂል በሙከራና በቁጥጥር ቡዱኖቹ መካካል ጉልህ ልዩነት እንዳልታየ የተገኘው ውጤት አመልክቷል፡፡

በትንተናዉ መሰረት የቁጥጥር ቡድን ተጠኚዎች ቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ዉጤት ከሙከራ ቡድን ተጠኚዎች ቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ዉጤት 3.5207 ብቻ እንደበለጠ ተረጋግጧል፡፡ መረጃዉ በባእድ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በሁለቱም ቡድኖች አማካይ ዉጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ዉጤቱ(ቲ=-1.539, የነጻነት ደረጃ= 60, የጉልህነት ደረጃ= 0.024) አሳይቷል፡፡ ይህም ማለት በ60 የነጻነት ደረጃ የሁለቱ ቡድኖች አማካይ ዉጤቶች የባለ ሁለት ጫፍ ልዩነት የጉልህነት ደረጃ (P value)= hp<2.44898 የበለጠ ነዉ፡፡ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የአማካይ ዉጤት ልዩነት አለ ለማለት የ"p" ዋጋ ከ0.05 ማነስ ነበረበት፡፡ በዚህ በባእድ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ስሌት መሰረት ሁለቱ ቡድኖች በተለያዩ ዘዴዎች ከመማራቸዉ በፊት የመጻፍ ክሂል ችሎታቸዉ ጉልህ ልዩነት እንደሌላቸዉ ተረጋግጧል፡፡

ከዚህ ዉጤት መረዳት የሚቻለዉ ከሙከራ በፊት በሁለቱም ቡድኖች የተመዘገበዉ የጉልህነት ዉጤት ከ0.05 በላይ በመሆኑ ተቀራራቢ የመጻፍ ክሂል ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ያሳያል፡፡ የተገኘዉ ዉጤትም በሁለቱ ቡድኖች ጥናቱን ማካሄድ እንደሚቻል ሊያመለክት ችሏል፡፡

ከቅድመ ፈተና ከተገኘዉ ዉጤት በመነሳት ለስድስት ሳምንታት ጥናቱ በከፊል ሙከራዊ ጥናት ዘዴ ተካሂዶ ሁለቱ ቡድኖች ድህረ የመጻፍ ክሂል ፈተና ተፈትነዋል፡፡ በዚህም ሂደት የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ዉጤት በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ዘዴ ተተንትነዋል፡፡

በተመሳሳይ መንገድ የሙከራ ቡድኑ 27 ተጠኚዎች ግብ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅሞ የመጻፍ ክሂል የተደገፈ ትምህርት በ10ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ከቀረቡት ምንባቦች መካከል የተመረጡትን የመጻፍ ክሂል መልመጃዎቻቸዉ ጋር በመዉሰድ ለስድስት ሳምንታት በየተመደቡበት ክፍል እንዲማሩ ተደርጎ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑ 35 ተጠኚዎች በተለመደዉ የማስተማሪያ ዘዴን በመጠቀም ከተማሩ በኋላ ሁለቱም ቡድኖች ከምንባቡ የወጣ አንድ ጥያቄ ፈተና ቀረበ፡፡

በድህረ ትምህርት የሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች ድህረ ትምህርት ፈተና ዉጤት አጠቃላይ ድምር(60.0926) ከቁጥጥር ቡድኑ ተጠኚዎች ድህረ ትምህርት ፈተና ዉጤት አጠቃላይ ድምር(52.0000) በ8.0926 ማርክ ብልጫ መሳየቱ፣ እንዲሁም የሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ዉጤት(60.0926) ከቁጥጥር ቡድኑ ተጠኚዎች ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ዉጤት(52.0000) በ8.0926 የአማካይ ዉጤት ብልጫ ማስመዝገባቸዉ ታዉቋል፡፡

መረጃዉ በጥንድ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ዉጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ዉጤቱ(ቲ-= -2.799,df=60,p=0.001) መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህም በ60 የነጻነት ደረጃ  የጉልህነት ደረጃ =0.001 ከp<0.05 ያነሰ ነዉ፡፡ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የአማካይ ዉጤት ልዩነት መኖሩን የ"p" ዋጋ ከ 0.05 አንሶ መገኘቱ ጠቋሚ ነዉ፡፡ ይህም የሚጠቁመዉ ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ሚና ያለዉ መሆኑ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ ጠቀሜታ ያለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ውጤቱም እነደሚያሳየው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ውጤት ጉልህ ልዩነት አሳይቷል፡፡

ከተገኘው ውጤት በመነሳት ጥናቱ ካስቀመጣቸው መላምቶች "ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ሚና አለው" የሚለው አቅጣጫ ጠቋሚ መላምት ተቀባይነት አግኝቶ "ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ሚና የለውም" የሚለው አቅጣጫ የለሽ መላምት ውድቅ ሆኗል፡፡

ስለዚህ ግብ ተኮር የማስተማሪያ ከተለመደዉ መጻፍን ከማስተማሪያ ዘዴ ቡድን ለቡድን ሲወዳደር ጉልህ ልዩነት ባያሳይም እያንዳንዳቸዉ ማስተማሪያ ዘዴዎች ውጤታማነታቸው በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ሲፈተሽ በግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የተማሩት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አንጻራዊ በሆነ መልኩ ጉልህ ልዩነት አሳይተዋል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ መደምደሚያ የመፍትሄ ሀሳቦች እና የጥናት ጥቆማዎች

### 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለማሻሻል ያለዉ ሚና መለየት ነዉ፡፡ ጥናቱ ምላሽ ሊሰጥበት ያነሳዉ መሰረታዊ ጥያቄ ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ሚና አለዉን? የሚልነዉ፡፡

ጥናቱ የተካሄደዉ በዳሪሙ ከተማ በሚገኘዉ የዳሪሙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነዉ፡፡የጥናቱ ተሳታፊዎች ደግሞ 2014 ዓ.ም ትምህርታቸዉን የሚከታተሉ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸዉ፡፡

በክፍል ደረጃዉ አምስት የመማሪያ ክፍሎች ዉስጥ ተመድበዉ የሚማሩ ሁለት መቶ አምሳ አንድ ተማሪዎች የሚማሩ ሲሆን ለጥናቱ የሚሆን ናሙና አስፈላጊ በመሆኑ ተራ የእጣ ንሞና ዘዴን በመጠቀም የምድብ 10-C እና 10- E ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ የተመረጡ ሲሆን በእነዚህ ክፍሎች የሚማሩ 96 ተማሪዎች በሙሉ በጠቅላይ ንሞና የጥናቱ ተሳታፊዎች ሆነዋል፡፡ነገር ግን ሰላሳ አራቱ ተማሪዎች ትምህርቱን አቋርጠዋል፡፡ የተቀሩት 62 ተማሪዎች ትምህርቱን በመከታተል ለጥናቱ ተሳታፊዎች ሆነዋል፡፡ ከሁለቱ ምድቦች በተራ የእጣ ንሞና ምድብ "C" የሙከራ ቡድን ሲሆን ምድብ "E' ደግሞ የቁጥጥር ቡድን ሆነዋል፡፡

የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ቅድመ እና ድህረ ፈተና ጥቅም ላይ ዉሏል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች ያላቸዉን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለመለካት የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍን መሰረት በማድረግ የተዘጋጁት ቅድመ እና ድህረ ፈተናዎች ለጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ከመቅረባቸዉ በፊት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አይተዉታል፡፡ ከዚያ ለጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

ተፈላጊዉ መረጃዎች ተሰብስበዉ ከተመዘገቡ በኋላ የሁለቱን ቡድን ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለማነጻጸር በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት ሲተነተን እያንዳንዱ ቡድን ከሙከራ በኋላ ያመጣዉን ለዉጥ ለመለየት በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡ ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ከተለመደዉ መጻፍን ከማስተማሪያ ዘዴ ቡድን ለቡድን ሲወዳደር ጉልህ ልዩነት ባይኖረዉም እያንዳንዳቸዉ የማስተማሪያ ዘዴዎች ዉጤታማነታቸዉ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ሲፈተሽ በግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የተማሩት የሙከራ ቡድን ተማረዎች ጉልህ ልዩነት ስላመጡ ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂል ችሎታን እንደሚያሻሽል ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የጥናቱ ዉጤት ግብ ተኮር የማሰተማሪያ ዘዴ በመማር ማስተማሩ ሂደት ቢተገበር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለማሻሻል እንደሚረዳ አመልክቷል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

ከጥናቱ ዉጤትና ማብራሪያ ማየት እደሚቻለዉ ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ከተለመደዉ መጻፍን ከማስተማሪያ ዘዴ ቡድን ለቡድን ሲነጻጸሩ ጉልህ ልዩነት ባይኖረዉም እያንዳንዳቸዉ የማስተማሪያ ዘዴዎች ዉጤታማነታቸዉ በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት እና በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ሲፈተሽ በግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የተማሩት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ጉልህ ልዩነት አሳይተዋል ፡፡ ስለዚህ ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለማሻሻል ሚና አለዉ ከሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሷል፡፡

## 5.3 የመፍትሄ ሀሳቦች

ከጥናቱ ዉጤት በመነሳት የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ይቻል ዘንድ የሚከተሉት የመፍትሄ ሀሳቦች ተሰጥተዋል፡፡

1. መምህራን ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ከመጻፍ ክሂል ችሎታ ጋር ያለዉን ቀጥተኛ ግንኙነት ተገንዝበዉ የመማር ማስተማሩን ሂደት በዚህ ዘዴ ቢተገብሩ የሚመለከታቸዉ አካላትም ክትትልና ድጋፍ ቢያደርጉ፡፡

2. ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል ሚና እዳለዉ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ በዚህም መሰረት በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ዉስጥ የሚዘጋጁ ተግባራት ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴን ከግምት ዉስጥ በማስገባት እንዲካተቱ የበለጠ ትኩረት ቢደረግባቸዉ፡፡

3. በዚህ የጥናት ዉጤት ላይ በመመስረት ከግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ በተጨማሪ በሌሎች የማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ መምህራንም ሆኑ ሌሎች የትምህርት ባለሙያዎች ጥናት ቢያካሂዱ፤ ለተማሪዎች የመጻፍ ክሂል መጎልበት የጎላ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ፡፡

## 5.4 የጥናቱ ጥቆማዎች

- ጥናቱ የተካሄደዉ በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ብቻ ስለሆነ በሌሎች የክፍል ደረጃዎች ላይም በግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ከፊል ሙከራዊ ጥናት ቢካሄድም አስፈላጊ እንደሆነ አጥኝዋ ታምናለች፡፡

- ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ከመጻፍ ክሂል በተጨማሪ ለሌሎች የአማርኛ ቋንቋ ክሂሎች የሚኖረዉ አስተዋጽኦ በከፊል ሙከራዊ ጥናት ሊፈተሽ እንደሚገባዉ አጥኝዋ ታምናለች፡፡

- በዚህ ጥናት የሙከራ ቡድኑ በድህረ ፈተና ያስመዘገበዉ አማካይ ዉጤት የቁጥጥር ቡድኑ ካስመዘገበዉ አማካይ ዉጤት በልጦ ቢገኝም ፤ልዩነቱ ጉልህ ቢሆንም ልምምዱ ሰፋ ያለ ጊዜ ተሰጥቶት ጥናት ቢካሄድ አስፈላጊ እንደሆነ አጥኝዋ ታምናለች፡፡

## ዋቢዎች

መላኩ ባይለየኝ (2013) ሂደት ተኮር መጻፍ ክሂል አቀራረብ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለዉ ሚና በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት፡፡ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡(ያልታተመ)

ማረው አለሙ፡፡ (2005)፡፡ በሳል ድርሰት ማስተማሪያ፡፡ ሁለተኛ እትም አዲስ አበባ ማተሚያ ድርጅት፡፡ አ-ኩራዝአሳታሚድርጅት

ማሬ አሰፋ፡፡ (2011)፡፡ችግር ፈቺ የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ያለው አስተዋጽኦ በዘጠነኛ ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ከፊል ሙከራዊ ጥናት በጎንደር ዩኒቨርሲቲ

በላይነህ አየነዉ፡፡ (2000)፡፡ ሂደታዊ የአጻጻፍ ብልሃት ለአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂልን ለማጎልበት ያለዉ ሚና፡፡ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ (ያልታተመ)

ተመስገን ፈቀደ፡፡ (2001)፡የ11ኛ ክፍል መምህራን የጽህፍት ክሂል ማስትማሪያ ዘዴና የተማሪዎች ድርሰት የመጻፍ ብለሃት ተዛምዶ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ቱሉ ንጉሱ (2014) የኦሮምኛ አፈ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ጽሁፍ ላይ የሚፈጽሟቸዉ ስህተቶች እና የስህተት ምንጭ ትንተና፡ (በጮራ ቦተር ወረዳ ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት) በጅማ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ (ያልታተመ)

አለምነሽአሰፋ (2011) ሂደታዊ የአጻጻፍ ዘዴን በመጠቀም ጽህፍትን ማስተማር የጽህፈትን ክሂል በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና (በደቡብ ክልል በከምባታ ጠምባሮ ዞን በሀደሮ ከተማ አስድደር ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማዎች ተተኳሪነት) ጅማ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ (ያልታተመ)፡፡

አማረ ተሸመ፡፡ (2010)፡፡ ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል እና ተነሳሽነት

አስተዋጽኦ ለማሻሻል ያለው ተጽእኖ፡፡ ለዶክተሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡አዲስአበባዩኒቨርሲ

አድማሱ አክሊሉና ደምሴ ማንያሎት፡፡ (1982)፡፡ ጥሩ የአማርኛ ድርሰት እንዴት ያለ ነው አዲስአበባ፤ ዩኒቨርሲቲ፡፡

እስከዳር ገቡየሁ፡፡ (2011)፡፡ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና በዘጠነኛ ክፍል ፈት- ተማሪዎች ተተኳሪነት፡፡ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጎንደርዩኒቨርሲቲ፡፡

የአምላክስራ ህይወት፡፡ (2008)፡፡ የአማርኛ አፈ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ጽሁፍ ላይ የሚፈጽሟቸው ሰህተቶች እና የስህተት ምንጭ ትንተና ፤ በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጡ ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፡ ለተግባራዊ  ስነልን አማርኛን ለማስተማር ኤም ኤ ድጊሪ ማሟያ የቀረበ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ያለው እዳወቀ (2011)፣ የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር ፣ሶስተኛ እትም ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ደረጀ ገብሬ እና ግርማ፡፡ (1999)፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ድርሰት የመጻፍ ብለሃት ተዛምዶ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

Byrne,D. (1988). Teaching Writing Skills. Hong Kong: Longman Group Ltd.

Byrne,(1997) . Teaching Writing Skills. London: Longman Group Ltd.

Clork,I. ( 2003). Concept in Composition theory Cend Practice in the teaching writing lawrecheah, Laboum assocated pliblisher, mchiwah New, Jersy; londen.

Ellis, R. (1994). <u>The study of second language acquisition</u>: oxford: oxford university

<u>File:///c:/users/hp/desktop/amharic%20thesis/unit_4.pdf</u>

<u>https://happynumbers.com/blog/list</u>-of-teaching-methodologies-primary-school/

Harmer, J. (1991).<u>The practice of English language teaching</u>. London: London group Ltd

Hedge, T. (1991). <u>Writing</u>. Oxford. Oxford university.

Kroll,B. (1990) .Second language writing Research in sight for the Class room Cambridge, Cambridge University Press.

Nunan, D. (1989). Designing tasks foer the communicative classroom. Cambrigde: cambrigde university press. International journal for infonomics(IJI), volume 13, issue 2, 2020)፡፡

Raimis, A. (1983). Techniques in the Teaching Writing. Oxford: Oxford University press.

Richards,J.C.(1974). Error Analysis Perspectives on Second Language Acquisition. London and Newyork: Longman Group Ltd.

Urevdu, A.A. (1985:22). Curriculum studies

Silva,T. (1993). Towards understanding writing. The ESL research and its implication. Joumal of second language writing: 2 p657-677

## አባሪ-1

**ለጥናቱ የቀረበ ቅድመ ትምህርት ፈተና**

የተማሪው ስም ----------------------ሴክሽን--------እድሜ--------እና መለያ ኮድ-----

ውድ ተፈታኞች ለትብብራችሁ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ ይህ ፈተና ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ያለው ሚና በሚል ርእስ ለሚሰራ ጥናት ለ 10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተንና ነው፡፡ ከዚህ በታች በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ለትምህርት ቤታችሁ የመታወቂያ ወረቀት እንዲሰጣችሁ ማመልከቻ ጻፉ፡፡

የተማሪው ስም ---------------------- ሴክሽን ---------- እድሜ -------- መ/ኮድ ---

መለያ ኮድ -----------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------

ይዘት ከ 25 -------------------

አደረጃጀት ከ 20 --------------------

ቃላት ከ 25 --------------------

የቋንቋ አጠቃቀም ከ 15 --------------------

ስርአተ ነጥብ ከ 15 ---------------------

ድምር ከ 100 ----------------------

## አባሪ-2

**ለጥናቱ የቀረበ ድህረ ትምህርት ፈተና**

የተማሪው ስም ---------------------ሴክሽን--------እድሜ--------እና መለያ ኮድ-----

ውድ ተፈታኞች ለትብብራችሁ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ ይህ ፈተና ግብ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ያለው ሚና በሚል ርእስ ለሚሰራ ጥናት ለ 10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና ነው፡፡

ከዚህ በታች በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ለትምህርት ቤታችሁ ሁለት አንቀጽ ባልበለጠ ማመልከቻ የሽኝ ደብዳቤ እንዲሰጣችሁ ጻፉ፡፡

የተማሪው ስም ------------------------- ሴክሽን ------ እድሜ ------ መ/ኮድ -----

መለያ ኮድ -----------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------

ይዘት ከ 25 -------------------

አደረጃጀት ከ 20 --------------------

ቃላት ከ 25 --------------------

የቋንቋ አጠቃቀም ከ 15 --------------------

ስርአተ ነጥብ ከ 15 ---------------------

ድምር ከ 100 ----------------------

## አባሪ-3

### የሙከራ ቡድን ቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ውጤት

| ቅድመ ፈተና<br>ምድብ አንድ | | | | ድህረ ፈተና<br>ምድብ አንድ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኮድ | አራሚ አንደ | አራሚ ሁለት | አማካይ | ኮድ | አራሚ አንደ | አራሚ ሁለት | አማካይ |
| C01 | 43 | 39 | 41.5 | C01 | 40 | 51 | 45.5 |
| C02 | 47 | 41 | 44 | C02 | 48 | 46 | 47 |
| C03 | 59 | 66 | 62.5 | C03 | 71 | 78 | 74.5 |
| C04 | 49 | 56 | 52.5 | C04 | 58 | 62 | 60 |
| C05 | 48 | 67 | 57.5 | C05 | 81 | 82 | 81.5 |
| C06 | 56 | 49 | 52.5 | C006 | 71 | 63 | 67 |
| C07 | 59 | 79 | 69 | C07 | 79 | 85 | 82 |
| C08 | 50 | 43 | 42.5 | C08 | 42 | 46 | 44 |
| C09 | 56 | 44 | 50 | C09 | 59 | 57 | 58 |
| C10 | 70 | 68 | 69 | C10 | 79 | 81 | 80 |
| C11 | 58 | 58 | 58 | C11 | 71 | 76 | 73.5 |
| C12 | 47 | 41 | 44 | C12 | 57 | 56 | 56.5 |
| C13 | 47 | 40 | 43.5 | C13 | 43 | 57 | 50 |
| C14 | 68 | 56 | 61 | C14 | 64 | 66 | 65 |
| C15 | 61 | 63 | 62 | C15 | 82 | 80 | 81 |
| C16 | 81 | 76 | 78.5 | C16 | 83 | 81 | 82 |
| C17 | 46 | 40 | 43 | C17 | 47 | 44 | 45.5 |
| C18 | 71 | 69 | 70 | C18 | 90 | 83 | 86.5 |
| C19 | 60 | 53 | 56.5 | C19 | 67 | 62 | 64.5 |
| C20 | 47 | 41 | 44 | C20 | 45 | 39 | 42 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| C21 | 50 | 49 | 49.5 | C21 | 61 | 68 | 64.5 |
| C22 | 54 | 59 | 56.5 | C22 | 44 | 39 | 41.5 |
| C23 | 41 | 35 | 38 | C23 | 45 | 40 | 42.5 |
| C24 | 54 | 47 | 50.5 | C24 | 45 | 49 | 47 |
| C25 | 49 | 46 | 47.5 | C25 | 45 | 45 | 45 |
| C26 | 57 | 58 | 57.5 | C26 | 49 | 57 | 53 |
| C27 | 53 | 49 | 51 | C27 | 46 | 40 | 43 |

አባሪ-4

**የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ውጤት**

| ቅድመ ፈተና<br>ምድብ አንድ | | | | ድህረ ፈተና<br>ምድብ አንድ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኮድ | አራሚ አንደ | አራሚ ሁለት | አማካይ | ኮድ | አራሚ አንደ | አራሚ ሁለት | አማካይ |
| E01 | 50 | 45 | 47.5 | E01 | 41 | 36 | 48.5 |
| E02 | 86 | 85 | 85.5 | E02 | 66 | 80 | 73 |
| E03 | 52 | 48 | 50 | E03 | 44 | 48 | 46 |
| E04 | 57 | 50 | 53.5 | E04 | 48 | 54 | 51 |
| E05 | 48 | 48 | 48 | E05 | 45 | 48 | 46.5 |
| E06 | 47 | 47 | 47 | E06 | 47 | 53 | 50 |
| E07 | 56 | 57 | 56.5 | E07 | 54 | 59 | 57 |
| E08 | 56 | 56 | 56 | E08 | 50 | 68 | 59 |
| E09 | 59 | 65 | 64 | E09 | 57 | 71 | 64 |
| E10 | 50 | 47 | 48.5 | E10 | 45 | 55 | 50 |
| E11 | 51 | 48 | 49.5 | E11 | 45 | 56 | 51 |
| E12 | 50 | 48 | 49 | E12 | 43 | 59 | 51 |
| E13 | 64 | 53 | 58.5 | E13 | 47 | 73 | 60 |
| E14 | 49 | 46 | 47.5 | E14 | 41 | 57 | 49 |
| E15 | 49 | 44 | 46.5 | E15 | 41 | 57 | 49 |
| E16 | 49 | 44 | 46.5 | E16 | 45 | 52 | 48.5 |
| E17 | 47 | 45 | 46 | E17 | 42 | 53 | 47.5 |
| E18 | 52 | 52 | 52 | E18 | 45 | 61 | 53 |
| E19 | 52 | 50 | 51 | E19 | 45 | 59 | 52 |
| E20 | 53 | 53 | 53 | E20 | 52 | 58 | 55 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| E21 | 49 | 45 | 47 | E21 | 40 | 58 | 49 |
| E22 | 45 | 40 | 42.5 | E22 | 41 | 48 | 43.5 |
| E23 | 49 | 51 | 50 | E23 | 50 | 55 | 52.5 |
| E24 | 51 | 46 | 48.5 | E24 | 41 | 58 | 49.5 |
| E25 | 46 | 53 | 49.5 | E25 | 53 | 46 | 49.5 |
| E26 | 46 | 41 | 43.5 | E26 | 44 | 46 | 45 |
| E27 | 54 | 61 | 57.5 | E27 | 70 | 68 | 69 |
| E28 | 48 | 44 | 46 | E28 | 43 | 61 | 52 |
| E29 | 44 | 42 | 43 | E29 | 42 | 58 | 50 |
| E30 | 45 | 45 | 45 | E30 | 45 | 63 | 54 |
| E31 | 48 | 45 | 46.5 | E31 | 41 | 59 | 50 |
| E32 | 46 | 44 | 45 | E32 | 42 | 62 | 52 |
| E33 | 41 | 37 | 39 | E33 | 51 | 51 | 51 |
| E34 | 49 | 47 | 48 | E34 | 47 | 49 | 48 |
| E35 | 49 | 48 | 48.5 | E35 | 50 | 50 | 50 |

መለያ ኮድ -018

ቀን፡ 16/09/2014

ጉዳዩ፡- የመተዳደሪያ ቅጣት/ቡራ ለደረሰኝ ለማስመለስ
- እኔ ተማሪ ሊድያን ካርሳ የዲሬክተር ወርቅ ሻይ ቤት ቅጥር ግቢ
ክዚ ከፊት እንደምታስገቡ ቅጣት ከገንዘብ ሲገባ ምን
ም ከቅጣት እንዲለቀቁ እና ቅጣር አይደለም፡፡
እንዳሰሩኝ በደ/ደረሰኝ እንዲመልሱልኝ ገለበሮት እጠይ
ቃለው፡፡

ክፍል 9ኛ 2C
ስም ሊድያን ካርሳ ፊርማ

| | ደረጃ አራሚ | ደረጃ ሁለት |
|---|---|---|
| ይዘት ከ 25 | 20 | 12 |
| ... ቋንቋ ከ 20 | 15 | 16 |
| ቅርፅ ከ 25 | 17 | 20 |
| የቋንቋ አጠቃቀም ከ 15 | 12 | 13 |
| ስርአተ ነጥብ ከ 15 | 7 | 8 |
| ድምር ከ 100 | 71 | 69 |

70

የሙከራ ቡድን ድህረ ትምህርት ፈተና በሁለት አራሚ

መለያ ኮድ 58 018

ቀን 29/9/2014

ለዳይሬክተር ወረዳ ዐይቀበሉ ጽ/ቤት

ጉዳዩ፦ የነዋሪነት መታወቂያ መጠየቅ ይሆናል፡፡

እኔ መሰለንግኝ ... ተማሪ ሔለን ከበደ ነዋሪነቴ በ... ቀበሌ ነው፡፡

የዚህ መልእክት ጉዳይ ... ለመታወቂያ ... ይሆናል፡፡ ... የነዋሪነት መታወቂያ ... ይጠበቃል፡፡

በመሆኑም ... ቀበሌ ... የነዋሪነት መታወቂያ ... እንዲሰጡኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

ከአክብሮት ጋር

ሔለን ከበደ

| | [illegible] | [illegible] |
|---|---|---|
| ይዘት ከ 25 | 22 | 20 |
| አደረጃጀት ከ 20 | 18 | 17 |
| ቃላት ከ 25 | 23 | 20 |
| የቋንቋ አጠቃቀም ከ 15 | 13 | 13 |
| ስርአተ ነጥብ ከ 15 | 14 | 13 |
| ድምር ከ 100 | 90 | 83 |

86.5

መለያ ኮድ --- 07

ጉዳዩ የመታወቂያ ወረቀት ስለመጠየቅ

ግንቦት - 15/09/2014

[illegible] ጽ/ቤት

[illegible]

[illegible]

[illegible]

ከሠላምታ ጋር

[illegible]

| | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት |
|---|---|---|
| ይዘት ከ 25 | 13 | 12 |
| አደረጃጀት ከ 20 | 14 | 15 |
| ቃላት ከ 25 | 10 | 12 |
| የቋንቋ አጠቃቀም ከ 15 | 10 | 10 |
| ስረአተ ነጥብ ከ 15 | 9 | 8 |
| ድምር ከ 100 | 56 | 57 |

56.5

መለያ ኮድ ---44--- 07

06/10/2014

ለዳይሬክተሩ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት

ጉዳዩ፡- የሽኝ ወረቀት ስለመጠየቅ ይሆናል።

ከላይ ለመግለፅ ያክል እንደ ተጠቀሰው ተማሪ [illegible] የተባልኩት ለዲሬክተሩ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ-ዎች ነበርኩ ይታወቃል።

ይሁን እንጂ አሁን በአገጠመኝ የግል ችግር ስላለኝ ወደ- [illegible] ለማዛወር ተገድጃለሁ ስለዚህ ይህንን ችግሬን ተረድታችሁ- ከለቀቃችሁኝ ደግፉ እንዲፈ እንድረዳ በእግዚአብሔር ስም- እጠይቃለሁ።

ከአክብሮት ጋር

[signature]

ተማሪ [illegible]

| | [illegible] | [illegible] |
|---|---|---|
| ይዘት ከ 25 | 13 | 15 |
| አደረጃጀት ከ 20 | 11 | 13 |
| ቃላት ከ 25 | 9 | 11 |
| የቋንቋ አጠቃቀም ከ 15 | 12 | 11 |
| ስርአተ ነጥብ ከ 15 | 9 | 9 |
| ድምር ከ 100 | 54 | 59 |

57